# አካባቢ ሳይንስ

## የተማሪ መጽሐፍ

## ፫ኛ ክፍል


አዘጋጆች

መለሰ ተካልኝ

በላይ አይዳኙህም

ብሩክ ለማ

አንዋር አወል

ዘሪቱ አባተ

አርታኢና ገምጋሚዎች፡

ሰሎሞን ወንድሙ

በላይ በለጠ

ሙሉነህ ተክለብርሃን

ጌታሁን ጌታቸው

ዓሊ ከማል

አስማምቶ አዘጋጆች፡-

አየለ ከበደ

መኮንን ውብሸት



ኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ትምህርት ቢሮ

# ምስጋና

ይህ መጽሐፍ በትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ ካርታ ምክረ ሐሳብ መሰረት በኢፌዲሪ ትምህርት ሚንስቴር ተዘጋጅተው የቀረቡትን የሥርዓተ ትምህርት መጽሐፍት ማዘጋጃ ሰነዶችን መነሻ በማድረግ በአዲስ አበባ ከተማ አስተደደር ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ የማስማማት ዝግጅት የተደረገበት ሲሆን የማስማማት ዝግጅቱና የሕትመት ወጪው በሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስትና በኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፕሮግራም-ኢ/GEQIP-E/ ተሸፍኖአል፡፡

በመሆኑም መጽሐፉን የማስማማት ዝግጅት ተደርጎበት መጠቀም እንዲቻል ለፈቀደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ፣ የማስማማት ዝግጅቱን በገንዘብ፣ በሰው ሃይልና በማቴሪያል፣ ልምዳቸውንና ዕውቀታቸውን በማጋራት ለረዱ፣እንዲሁም ሌሎችም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለደገፉ አካላት፣ተቋማትና ግለሰቦች ሁሉ የሲዳማ ትምህርት ቢሮ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡

# ©የቅጂ መብት.

የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት የአዲስ አበባ አስተዳደርና የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ትምህርት ቢሮዎች ናቸው፡፡

© 2014፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ድሞክራሳዊ ሪፓብልክ ትምህርት ሚኒስቴር፤ የቅጂ መብት ሙሉ የተከበረ ነው፡፡ ያለፈቃድ ማተም፣ ማባዛት፣ ባልተገባ መንገድ ማከማቸትና በሃርድ ኮፒም ሆነ በሶፍት ኮፒ ማሰረጨት እንዲሁም ላልተገባ ዓላማ መጠቀም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ድሞክራሳዊ ሪፓብልክ፤ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 410/2004 ቅጂ መብት እና ጥበቃ ደንብ መሰረት ያስቀጣል፡፡

የመጀምሪያ እትም 2016 ዓ.ም
ሲዳማ/ ሃዋሳ

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**

ምዕራፍ አንድ፡ የወረዳችን መገኛ ........ 1

1.1. የአንጻራዊ መገኛ ምንነት ........ 2

1.2 የፍጹማዊ መገኛ ምንነት ........ 5

1.3 የወረዳችን አንጻራዊ መገኛ ........ 10

1.4 የወረዳችን ፍጹማዊ መገኛ ........ 12

1.5. በወረዳችን የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎች መገኛ ........ 13

1.6. የወረዳችን አዋሳኝ ወረዳዎች መገኛና ስማቸው ........ 14

ማጠቃለያ ........ 16

የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች ........ 17

ፍተሻ ........ 19

ምዕራፍ ሁለት፡ ሳይንስን መገንዘብ ........ 20

መግቢያ ........ 21

2.1. ምግብና ጤና ........ 21

2.2. የምግብ ጠቀሜታ ........ 25

2.3. የግል ንፅሕና አጠባበቅ ........ 31

2.4. የቁስ አካል አካላዊ ለውጦች ........ 40

2.5. የብርሃን ጠቀሜታ ........ 45

ማጠቃለያ ........ 49

የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች ........ 50

ፍተሻ ........ 52

ምዕራፍ ሦስት፡ ተፈጥሮአዊ አካባቢ 53
መግቢያ 55
3.1. የወረዳችን አየር ንብረት 55
3.2. የተፈጥሮ ሀብቶች 59
3.3 የተፈጥሮ ሀብቶች ለወረዳችሁ ህልውናና ዕድገት ያለው ፋይዳ 66
3.4. በትምህርት ቤትና በቀበሌያችሁ የሚስተዋሉ ተገቢና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች 73
3.5 ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ተፅዕኖዎች 76
ማጠቃለያ 80
የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች 81
ፍተሻ 83

ምዕራፍ አራት፡ ማኅበራዊ አካባቢ 84
መግቢያ 85
4.1 የባህል ብዝኀነት 85
4.2 በወረዳችሁ የሚገኙ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች 95
ማጠቃለያ 113
የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች 114
ፍተሻ 117

ምዕራፍ አምስት፡ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች ........ 118

መግቢያ ........ 118

5.1. የመንገድ ደኅንነት ........ 119

5.2. ኤች. አይ. ቪ. / ኤድስ ........ 131

ማጠቃለያ ........ 135

የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች ........ 136

ፍተሻ ........ 138

# ምዕራፍ አንድ

# የወረዳችን መገኛ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

**ተማሪዎች! ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦**

- አቅጣጫን የመለየት ክህሎት ታዳብራላችሁ፡፡
- ሥዕሎችንና ካርታዎችን በመጠቀም ከሰዎች ጋር ለመግባባት ፈቃደኝነታችሁን ታሳያላችሁ፡፡
- የአንጻራዊ መገኛን ምንነትን ትገልፃላችሁ፡፡
- የፍጹማዊ መገኛን ምንነት ትገልፃላችሁ፡፡
- የወረዳችሁን አንጻራዊ መገኛ ማመልከት፡፡
- በካርታ ላይ ኬክሮስና ኬንትሮስን በመጠቀም የወረዳችሁን መገኛ ታመለክታላችሁ፡፡
- በወረዳችሁ የሚገኙ ቁልፍ ቦታዎችን ለማመልከት ኬክሮስና ኬንትሮስን ትጠቀማላችሁ፡፡
- የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ በመጠቀም በወረዳችሁ የሚገኙ ቦታዎችን ታመለክታላችሁ፡፡

### የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች

1.1. የአንጻራዊ መገኛ ምንነት
1.2. የፍጹማዊ መገኛ ምንነት
1.3. የወረዳችን አንጻራዊ መገኛ
1.4. የወረዳችን ፍጹማዊ መገኛ
1.5. በወረዳችን የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎች መገኛ
1.6. የወረዳችን አዋሳኝ ወረዳዎች መገኛና ስማቸው

# መግቢያ

ተማሪዎች! በሁለተኛ ክፍል ስለቀበሌያችሁ ምንነትና መገኛ ተምራችኋል፡፡ በሦስተኛ ክፍል ደግሞ ስለአንጻራዊ መገኛ ምንነት፣ ስለፍጹማዊ መገኛ ምንነት፣ ስለወረዳችሁ አንጻራዊ መገኛና ፍጹማዊ መገኛ፣ በወረዳችሁ ስለሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎች መገኛና ስለወረዳችሁ አዋሳኝ ወረዳዎች መገኛና ስማቸውን ትማራላችሁ፡፡

ወረዳ የተለያዩ ቀበሌያትን የያዘ የአስተዳደር እርከን ነው፡፡
ከተማ አስተዳደር የተለያዩ ክፍለ ከተሞችን በውስጡ የያዘ የአስተዳደር እርከን ነው፡፡ ክፍለ ከተማ ደግሞ የተለያዩ ቀበሌያትን የያዘ የአስተዳደር እርከን ነው፡፡
በሲዳማ ክልል ሰላሳ ወረዳዎች እና ሰባት ከተማ አስተዳደሮች ይገኛሉ፡፡

እነርሱም፡- 1ኛ. ወረዳዎች

አለታ ጩኮ፣ አለታ ወንዶ፣ አርቤጎና፣ አሮሬሳ፣ ሃዋሳ ዙሪያ፣ በንሳ፣ ሀዌላ፣ ቦና ዙሪያ፣ ቦሪቻ፣ ቡርሳ፣ ጭሬ፣ ዳሌ፣ ዳራ፣ ጎርቼ፣ ብላቴ ዙሪያ፣ ደራራ፣ ሎካ አባያ፣ ማልጋ፣ ሽበዲኖ፣ ወንሾ፣ ዳራ ኦቲልቾ፣ ሁላ፣ ጭሮኔ፣ ጢጢቻ፣ ሻፋሞ፣ ቡራ፣ ጨቤ ጋምቤልቶ፣ ሆኮ፣ ዳኤላ እና ወንዶ ገነት ወረዳዎች ናቸው፡፡

2ኛ. ከተማ አስተዳደሮች

ሀዋሳ፣ ወንዶ ገነት፣ ለኩ፣ ይርጋለም፣ አለታ ጩኮ፣ አለታ ወንዶ እና ዳዬ ከተማ አስተዳደሮች ናቸው፡፡

## 1.1. የአንጻራዊ መገኛ ምንነት


### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- የአንጻራዊ መገኛን ምንነትን ትገልጻላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃል**

- አንጻራዊ መገኛ
- ወረዳ




ሥዕል 1. መሠረታዊ አቅጣጫዎች

ተግባር 1.

የተግባር ሥራ

ዓላማ:- አንጻራዊ መገኛን መግለጽ

መመሪያ:- ተማሪዎች 5 በመሆን ቡድን በመመስረት ከታች በቀረበው ጥያቄ ላይ መልሳቸሁን በክፍል ውስጥ በተግባር አሳዩ።

የመወያያ ጥያቄ:-

1. አራቱን መሰረታዊ አቅጣጫዎች የአካል ክፍላችሁን በመጠቀም ለመምህራችሁ አሳዩ።

## ሀ. አራቱ መሠረታዊ አቅጣጫዎች

አራቱ መሠረታዊ አቅጣጫዎች የሚባሉት ሰሜን ፣ ደቡብ ፣ ምዕራብና ምሥራቅ ናቸው። እነዚህን አቅጣጫዎች በመጠቀም የአንድን ነገር አንጻራዊ መገኛ ማመልከት ይቻላል።

**አንጻራዊ መገኛ** አንድ ነገር የት እንደሚገኝ ከአካባቢው ካሉ ታዋቂ ቦታዎች ጋር በማነፃፀር የምንገልጽበት አንዱ ዘዴ ነው።

ለምሣሌ፡- ሕንፃዎች፣ ሀዉልቶች፣ ወንዞች፣ ተራራዎች፣ መንገዶችና የመሳሰሉት


ተግባር 2

ዓላአንጻራዊ መገኛን መግለጽ።

መመሪያ፡- ተማሪዎች! አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት ከታች የቀረበውን ሥዕል በመመልከት መልሳቸሁን በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

ኳስ ተጨዋቾች





ትምህርት ቤት






1. ትምህርት ቤቱ ከኳስ ተጨዋቾች በስተየት ይገኛል?
2. ሆስፒታሉ የት ይገኛል?
3. ኳስ ተጨዋቾች ከትምህርት ቤቱ በስተየት ይገኛሉ?

## 1.2 የፍጹማዊ መገኛ ምንነት


### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- የፍጹማዊ መገኛ ምንነትን ትገልፃላችሁ።

**ቁልፍ ቃላት፦**

- ፍጹማዊ መገኛ
- ኬክሮስ
- ኬንትሮስ
- ቋሚ መስመሮች
- ተጓዳኝ መስመሮች




ሥዕል 2 በሉል ላይ ያሉ የሀሳብ መስመሮች ስያሜ

የቡድን ውይይት 1.

ዓላማ:- የፍጹማዊ መገኛ ምንነትን መለየት

መመሪያ:- ተማሪዎች! አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት ከታች በቀረበው ጥያቄ ላይ በመወያየት መልሳችሁን በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

የመወያያ ጥያቄዎች:

1. ፍጹማዊ መገኛ ምንድን ነው?
2. ኬክሮስ ምንድን ነው?
3. ኬንትሮስ ምንድን ነው?

**ፍጹማዊ መገኛ** ማለት ኬክሮስና ኬንትሮስን በመጠቀም የአንድን ነገር ትክክለኛ መገኛ የምናመለክትበት ዘዴ ነው።

ኬንትሮስ ማለት ከመነሻ ዋልታ በስተምሥራቅና በስተምዕራብ በቋሚ መስመሮች መካከል ያለውን ርቀት የሚለካ እና ርቀቱን በዲግሪ የሚገልጽ ልኬት ነው። የኬንትሮስ መለኪያዎች ዜሮ ዲግሪን (ፐራይም ሜሪዲያን ) መነሻ በማድረግ ወደ ምሥራቅ 180 ዲግሪ እና ወደ ምዕራብ 180 ዲግሪ ይለካሉ። በአጠቃላይ 360 ዲግሪ ይለካሉ።

**ዜሮ ዲግሪ ኬንትሮስ** (መነሻ ዋልታ) መሬትን ምሥራቃዊና ምዕራባዊ ንፍቀ ክበብ በማለት እኩል ቦታ የሚከፍል መነሻ ቦታ ነው።

**ቋሚ መስመር** በካርታ ላይ ተመሣሣይ ኬንትሮስ ያላቸውን ቦታዎች የሚያገናኝ የሀሳብ መስመር ነው። ሁሉም ቋሚ መስመሮች ከሰሜን ወደ ደቡብ ይሰመራሉ። ቋሚ መስመሮች ከመነሻ ዋልታ 180 ዲግሪ ወደ ምሥራቅና 180 ዲግሪ ወደ ምዕራብ ይዘረጋሉ።

**ኬክሮስ** ማለት ከምድር ወገብ ሰሜንና ደቡብ በተጓዳኝ መስመሮች መካከል ያለውን ርቀት የሚለካ እና ርቀቱም በዲግሪ የሚገለፅ ልኬት ነው። ከዜሮ ዲግሪ የምድር ወገብ

ወደ ሰሜን 90 ዲግሪ እና ወደ ደቡብ 90 ዲግሪ የሚለኩ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ 180 ዲግሪ ይለካሉ፡፡

የምድር ወገብ (ዜሮ ዲግሪ ኬክሮስ) መሬትን ሰሜናዊና ደቡባዊ ንፍቀ-ክበብ በማለት እኩል ቦታ የሚከፍል መነሻ ቦታ ነው፡፡


ተጓዳኝ መስመሮች እርስ በርሳቸው የማይቋረጡ ተመሳሳይ ኬክሮስ ያላቸውን ቦታዎች የሚያገናኙ የሀሳብ መስመሮች ናቸው፡፡ ሁሉም ተጓዳኝ መስመሮች ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ወይም ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ይሰመራሉ፡፡ ከምድር ወገብ ወደ ሰሜን 90 ዲግሪና ከምድር ወገብ ወደ ደቡብ 90 ዲግሪ ድረስ ይዘረጋሉ፡፡

የቡድን ውይይት 2.

ዓላማ፡- አንጻራዊ መገኛን መግለጽ።

መመሪያ፡- ተማሪዎች! አምስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ከታች የቀረበላችሁን ሥዕል በመመልከት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ።

1. ፊደል ሀ  ምንን ያመለክታል?
2. ፊደል ለ  ምንን ያመለክታል?
3. ፊደል ሐ  ምንን ያመለክታል?
4. ፊደል መ ምንን ያመለክታል?



## መልመጃ 1

ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች በማንበብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ

1. አንጻራዊ መገኛ የአንድን ቦታ መገኛ ለመግለፅ ይጠቅማል፡፡
2. መሰረታዊ አቅጣጫዎች የቦታዎችን መገኛ ለማወቅ ይጠቅማሉ፡፡
3. ፍጹማዊ መገኛ ኬክሮስና ኬንትሮስን ለመለካት ይጠቀማል፡፡

ለ. በ 'ሀ' ስር የቀረቡትን መግለጫዎች በ 'ለ' ስር ከተዘረዘሩት አማራጮች ጋር በትክክል አዛምዱ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ተመሳሳይ ኬክሮስ ያላቸውን ቦታዎች የሚገናኝ መስመር | ሀ. ቋሚ መስመር |
| 2. ምስራቅና ምዕራብ ንፍቀ-ክበብን የሚለኩ | ለ. ተጓዳኝ መስመር |
| 3. ተመሳሳይ ኬንትሮስ ያላቸውን ቦታዎች የሚያገናኝ | ሐ. ኬክሮስ |
| 4. ሰሜንና ደቡብ ንፍቀ-ክበብን የሚለኩ | መ. ኬንትሮስ |

ሐ. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተገቢው መልስ ሙሉ፡፡

1. መሬትን ሰሜናዊና ደቡባዊ ንፍቀ-ክበብ በማለት እኩል ቦታ የሚከፍለው -------------ነው፡፡
2. መሬትን ምዕራባዊና ምስራቃዊ ንፍቀ-ክበብ በማለት እኩል ቦታ የሚከፍለው -------------ነው፡፡

መ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. ኬንትሮስ ከየት ወደ የት ይለካል? አጠቃላይ ልኬቱ ስንት ነው?

2. ኬክሮስ ከየት ወደ የት ይለካል? አጠቃላይ ልኬቱ ስንት ነው?

## 1.3 የወረዳችሁ አንጻራዊ መገኛ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- የወረዳችሁን አንጻራዊ መገኛ ታመለክታላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- አንጻራዊ መገኛ
- ወረዳ


የቡድን ውይይት 3

ዓላማ፡- የወረዳችንን አቅጣጫ መለየት

መመሪያ፡- ተማሪዎች! አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት ከታች በቀረቡት ጥያቄ ላይ በመወያየት መልሳችሁን በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች፡

1. ትምህርት ቤታችሁ በየትኛው ወረዳ እንደሚገኝ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ትምህርት ቤታችሁ የሚገኝበት ወረዳ ከሌሎች አዋሳኝ ወረዳዎች አንጻር በስተየት ይገኛል?



ሥዕል 3 የሲዳማ ክልል ካርታ

ተግባር 3.

ዓላማ፡- የወረዳችሁን አንፃራዊ መገኛ ማመልከት

መመሪያ፡- ተማሪዎች! አምስት በመሆን ቡድን በመመስረት ከታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት መልሳችሁን በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

1. ተማሪዎች በቡድናችሁ በመሆን የሲዳማ ክልል ንድፍ ካርታ በራሳችሁ አዘጋጅታችሁ ለመምህራችሁ አስረክቡ፡፡

## መልመጃ 2.

ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. አራቱን መሠረታዊ አቅጣጫዎች ፃፉ፡፡
2. የራሳችሁን ወረዳ አንጻራዊ መገኛን አስቀምጡ፡፡

## 1.4 የወረዳችን ፍጹማዊ መገኛ


ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፥

በካርታ ላይ ኬክሮስና ኬንትሮስን በመጠቀም የወረዳችሁን ፍጹማዊ መገኛ ታመለክታላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ፍጹማዊ መገኛ
- ወረዳ
- ኬክሮስ
- ኬንትሮስ



ሥዕል 4. የሲዳማ ክልል ካርታ

ተግባር 4.

ዓላማ፡ የወረዳቸውን ፍጹማዊ መገኛ ማመልከት

መመሪያ፡- ተማሪዎች! ሥዕል 4ን በመጠቀም የወረዳችሁን ፍጹማዊ መገኛ አመልክቱ::

በሲዳማ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወረዳዎች የራሳቸው የሆነ ፍጽማዊ መገኛ አላቸው::

## 1.5. በወረዳችን የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎች መገኛ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

በወረዳችሁ የሚገኙ ቁልፍ ቦታዎችን ኬክሮስና ኬንትሮስን በመጠቀም ታመለክታላችሁ::

ቁልፍ ቃላት

- ቁልፍ ቦታዎች
- ኬክሮስ
- ኬንትሮስ

ተግባር 5.

ዓላማ፡ በወረዳችሁ የሚገኙ ቁልፍ ቦታዎችን ኬክሮስና ኬንትሮስ በመጠቀም ማመልከት

መመሪያ፡-ተማሪዎች! ከሥዕል 4 ካርታ ላይ በመመልከት በወረዳችሁ የሚገኙ ቁልፍ ቦታዎችን ፍጹማዊ መገኛ አመልክቱ::

በወረዳችን የሚገኙ ቁልፍ ቦታዎች ጤና ጣቢያ፣ ፖሊስ ጣቢያ፣ ትምህርት ቤት፣ ቀበሌያትና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል። የእነዚህን ቁልፍ ቦታዎች ፍጹማዊ መገኛ ማወቅና ማመልከት ይቻላል።

## 1.6. የወረዳችን አዋሳኝ ወረዳዎች መገኛና ስማቸው

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያን በመጠቀም በወረዳችሁ የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎችን ታመለክታላችሁ።

**ቁልፍ ቃላት**

- የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ





ሥዕል 5 የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ

ተግባር 6.

ዓላማ፦ የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ እንዲጠቀሙ ማድረግ።

መመሪያ፦ ተማሪዎች! በየግላችሁ የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያውን አጠቃቀም በመለማመድ በክፍል ውስጥ በሚቀርብላችሁ መተግበሪያ ቁልፍ ቦታዎችን ለመምህራችሁ አሳዩ።



ሥዕል 6 ሰዎች የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ ሲጠቀሙ

የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ ማለት ሰዎች ማግኘት የሚፈልጉትን ቦታ የጎግል ድህረ-ገፅ ተጠቅመው በመፈለግ ቦታው በቀላሉ የት እንደሚገኝ የሚያመለክት መተግበሪያ ነው።

የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ ጥቅም

- የአንድን ቦታ ትክክለኛ መገኛ ይነግረናል።
- ተጠቃሚዎች ጓደኛማዊነት ግንኙነት እንዲኖራቸው ያደርጋል።
- ለምንጠይቀው ጥያቄ በፍጥነት መልስ ይሰጠናል።

## ማጠቃለያ

- አንጻራዊ መገኛ አንድ ነገር የት እንደሚገኝ ከአካባቢው ካሉ ታዋቂ ቦታዎች አንፃር የምንገልፅበት መንገድ ነው።
- አራቱ መሠረታዊ አቅጣጫዎች የሚባሉት ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምዕራብና ምሥራቅ ናቸው።
- ፍጹማዊ መገኛ ኬክሮስና ኬንትሮስን በመጠቀም የአንድን ቦታ ትክክለኛ መገኛ የሚያሳይ ነው።

ወረዳ የተለያዩ ቀበሌያትን የያዘ የአስተዳደር እርከን ነው።

ከተማ አስተዳደር የተለያዩ ክፍል ከተሞችን በውስጡ የያዘ የአስተዳደር እርከን ነው።

- በሲዳማ ክልል ውስጥ ሰላሳ ወረዳዎችና ሰባት ከተማ አስተዳደሮች አሉ።
- ኬንትሮስ ማለት ከመነሻ ዋልታ በስተምሥራቅና በስተምዕራብ በቋሚ መስመሮች መካከል ያለውን ርቀት የሚለካ እና ልኬቱም በዲግሪ የሚገለፅ ነው።
- ኬክሮስ ማለት ከምድር ወገብ ሰሜንና ደቡብ በተጓዳኝ መስመሮች መካከል ያለውን ርቀት የሚለካ እና በዲግሪ የሚገለፅ ነው።
- የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ ሰዎች ማግኘት የሚፈልጉትን ቦታ የጎግል ድህረ-ገፅ ተጠቅመው በመፈለግ ቦታው በቀላሉ የት እንደሚገኝ የሚያመለክታቸው መተግበሪያ ነው።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች በማንበብ ትክክል ከሆነ “እውነት” ትክክል ካልሆነ “ሐሰት” በማለት መልሱ።**

1. አንጻራዊ መገኛ የወረዳችንን መገኛ ለማወቅ ይረዳናል።
2. ሁሉም ወረዳዎች ፍጹማዊ መገኛ የላቸውም።
3. በጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ ቦታዎች የት እንደሚገኙ ማወቅ ይቻላል።
4. የወረዳችንን አንጻራዊ መገኛ ለማወቅ በአካባቢው ያሉትን ወረዳዎች ማወቅ ይኖርብናል።
5. ፍጹማዊ መገኛ ኬክሮስና ኬንትሮስን ይጠቀማል።

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።**

1. ከሚከተሉት ወረዳዎች ውስጥ በሲዳማ ክልል የማይገኘው የትኛው ነው?

   ሀ. ቦና ለ. ሎካ አባያ ሐ. ዲላ መ. ደራራ

2. መሬትን ምሥራቅ ንፍቀ-ክበብና ምዕራብ ንፍቀ-ክበብ በማለት የሚከፍለው የትኛው ነው?

   ሀ. ኬክሮስ ለ. ጎግል ካርታ ሐ. ኬንትሮስ መ. መነሻ ዋልታ

3. የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳደር ጽሕፈት ቤት በየትኛው ከተማ አስተዳደር ይገኛል?

   ሀ. ይርጋለም ለ. ለኩ ሐ. ዳዬ መ. ሀዋሳ

4. በወረዳችሁ ውስጥ የሚገኘው ቁልፍ ቦታ የቱ ነው?

ሀ. ቀበሌ ለ. ትምህርት ቤት ሐ. ጤና ጣቢያ መ. ሁሉም

## ሐ. የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች በተገቢው መልስ ሙሉ፡፡

1. የመሬት ሰሜን እና ደቡብ ንፍቀ-ክበብ መነሻ ቦታ---------------ይባላል፡፡
2. ተመሳሳይ ኬክሮስ ያላቸውን ቦታዎች የሚያገናኝ የሀሳብ መስመር----- በመባል ይታወቃል፡፡

## መ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ

1. በወረዳችሁ ከሚገኙ ቁልፍ ቦታዎች መካከል ቢያንስ ሁለቱን ጥቀሱ፡፡
2. የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ ለምን ይጠቅማል ?

## ፍተሻ

የምታውቋቸውን ክንውኖች በመለየት በእያንዳንዱ ሳጥን ውስጥ ይህንን (✓) ምልክት አስቀምጡ

1. አቅጣጫን የመለየት ክህሎት አዳብሪያለሁ፡፡ ☐
2. ሥዕላትንና ካርታዎችን በመጠቀም ከሰዎች ጋር ለመግባባት ፈቃደኝነት አሳያለሁ፡፡ ☐
3. የአንጻራዊ መገኛን ምንነትን እገልጻለሁ፡፡ ☐
4. የፍጹማዊ መገኛን ምንነትን እገልጻለሁ፡፡ ☐
5. የወረዳችንን አንጻራዊ መገኛ አመለክታለሁ፡፡ ☐
6. በካርታ ላይ ኬክሮስና ኬንትሮስን በመጠቀም የወረዳዬን መገኛ አመለክታለሁ፡፡ ☐
7. በወረዳችን የሚገኙ ቁልፍ ቦታዎችን ለማመልከት ኬክሮስና ኬንትሮስን መጠቀም እችላለሁ፡፡ ☐
8. የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ በመጠቀም በወረዳዬ የሚገኙ ቦታዎችን አመለክታለሁ፡፡ ☐

# ምዕራፍ ሁለት

# ሳይንስን መገንዘብ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ጤናማ ምግቦችና መጠጦችን ትለያላችሁ።
- ምግቦችን በአራት መሠረታዊ ምድቦች ትከፍላላችሁ።
- የምግብ ብክለትን ለመከላከል የሚያስችሉ የንፅሕና አጠባበቅ መንገዶችን ትለያላችሁ
- የንጽህና መጠበቂያ መንገዶችን ትገልጻላችሁ።
- የጠጣር፣ ፈሳሽና ጋዞች ባሕርያትን ፍችዎች ትገልጻላችሁ።
- የጠጣር፣ የፈሳሽና የጋዝ ባሕሪያትን በመስጠት የቁስ አካላትን (የጠጣር ፣ ፈሳሽና የጋዝ) የሁነታ ለውጥ ትገልጻላችሁ።
- የብርሃንን ጥቅሞች ትዘረዝራላችሁ።

የትምህርቱ ዋና ዋና ይዘቶች፦

2.1. ምግብና ጤና

2.2. የምግብ ጠቀሜታ

2.3. የግል ንፅሕና አጠባበቅ

2.4. የቁስ አካል አካላዊ ለውጥ

2.5. የብርሃን ጠቀሜታ

### መግቢያ

ተማሪዎች! በሁለተኛ ክፍል ስለምግብ ጥቅሞች፣ ስለብርሃን ምንነት፣ስለ ብርሃን ምንጮችና ስለ ቁስ አካል ባህሪያት ተምራችኋል። በሦስተኛ ክፍል ደግሞ ስለምግብና ጤና ፣ ስለምግብ ጥቅም ፣ስለምግብ ብክለት መንስኤዎች ፣ ስለግል ንፅህና አጠባበቅ ፣ ስለቁስ አካላት ሁነቶች እና የብርሃን ጥቅሞች ትማራላችሁ።

ምግብ ሰውነትን ለመገንባት፣ የተጎዱ አካሎቻችንን ለመጠገን፣ ከተለያዩ በሽታዎች ለመከላከልና ጉልበት ለማግኘት ይጠቅመናል። የሰው ልጅ ጤንነቱን ለመጠበቅ ማድረግ ከሚገባው ነገሮች አንዱ ምግብን በጥንቃቄ መያዝና መመገብ ነው። የግልና የአካባቢያችንን ንፅሕና በመጠበቅ ራስን ከበሽታ መከላከል ይቻላል።

በትምህርቱም ሂደት እንደ መመልከት ፣ መጠየቅ ፣ ስዕላዊ መግለጫዎችን መተርጎም መግባባትና ተባብሮ መሥራት የመሳሰሉትን የሳይንሳዊ ምርምር ክህሎቶችን ታዳብራላችሁ። ስለሆነም ለትምህርታችሁ ትኩረት በመስጠት በንቃት እየተሳተፋችሁ መማር ይጠበቅባችኃል።


## 2.1. ምግብና ጤና

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡

- ጤናማ ምግቦችና መጠጦችን ትለያላችሁ።









ሥዕል1 ሀ ጤናማ ያልሆኑ ምግቦች

ለ ጤናማ የሆኑ ምግቦች

**ቁልፍ ቃላት**

- ምግብ
- ጤና

ተግባር 1

ጭውውት

ዓላማ፦ ጤናማ ምግቦችና መጠጦችን መለየት

መመሪያ፦ ተማሪዎች! አራት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የጤናማ ምግቦችና መጠጦችን አዘገጃጀት፣ አቀማመጥና አመጋገብ የሚያሳይ አጭር ጭውውት አዘጋጅታችሁ በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

## ምግብ

ማንኛውም ሊበላ ወይም ሊጠጣ የሚችልና ለሰውነት ጠቃሚ ነገር ነው። በህይወት ለመኖር ከሚያስፈልጉት መሠረታዊ ነገሮች አንዱ ነው። ሰውነትን ለመገንባትና ለመጠገን፣ ከበሽታዎች ለመከላከል፣ ጉልበትና ሀይል ለመስጠት ይጠቅማል።

## ጤና

አካላዊ፣ አእምሮአዊና ማኅበራዊ ደኅንነት ማለት ነው። ጤናማ ለመሆን ጤናማ ምግብ መመገብ ይኖርብናል።

ጤናማ ምግብ ማለት ከበሽታ አምጪ ተህዋስያንና ከሌሎች ጎጂ ነገሮች ነፃ የሆነ ምግብ ነው። ጤናማ የሆነ ምግብ ያልተለመደ ጠረንና ጣዕም እንዲሁም ለዕይታ የተለየ መልክ የለውም። ምሣሌ ያልተበላሸ ወጥ፣ ያልሻገተ እንጀራ፣ ንፁህ እንቁላል ፣ ንጹህ ፍራፍሬ፣ የፈላ ወተት፣ የበሰለ ሥጋ እና የመሳሰሉት ናቸው።

ጤናማ ያልሆነ ምግብ ማለት በሽታ አምጪ ተህዋስያንና በሌሎች ጎጂ ነገሮች የተበከለ ምግብ ነው። ጤናማ ያልሆነ ምግብ ያልተለመደ ጠረንና ጣዕም እንዲሁም ለእይታ የተለየ መልክ ሊፈጥር ይችላል። ለምሳሌ የገማ እንቁላል፣ የተበላሸ የምስር ወጥ፣ የሻገተ እንጀራ፣ የተበላሸ ሙዝና የመሳሰሉት ናቸው።



ምግብን በማቀዝቀዝ　　ምግብን በማሸግ　　ምግብን በማድረቅ

ሥዕል 2. የምግብ ማቆያ ዘዴዎች

የምንመገበው ምግብ በጥንቃቄ ካልተያዘ በዐይን በማይታዩ ጥቃቅን ተህዋስያን ሊበከሉ ይችላሉ። በመሆኑም ምግብ ሲዘጋጅም ሆነ ሲቀመጥ በጥንቃቄ መሆን አለበት። በዐይን የማይታዩ ጥቃቅን ተህዋስያን ምግባችንን እንዳያበላሹና ለበሽታ እንዳያጋልጡን መከላከል የምንችልባቸው ዘዴዎች አሉ።

ለምሳሌ፡- ውሃን ማፍላት፣ ምግብን በማቀዝቀዣ ውስጥ ማቆየት፣ ምግብን በደንብ ማብሰል፣ ማድረቅ፣ ጨው መነስነስና የመሳሰሉት ናቸው።

## መልመጃ 2.1.

ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች በማንበብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ፣ ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ::

1. ወተትን አፍልቶ መጠጣት ተገቢ ነው::
2. ምግብን በማብሰል ጎጂ ተህዋስያንን መግደል እንችላለን::
3. ምግብ ሳይበላሽ ረዘም ላለ ጊዜ እንዲቆይ ማድረግ ይቻላል::
4. ያልተለመደ ሽታ ያለው ምግብን መብላት የለብንም::
5. በሽታ ሊያመጡ የሚችሉ ተህዋስያን በምግብ ውስጥ ሊኖሩ አይችሉም::

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ::

1. ጤናማ ምግብ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ጤናማ ያልሆነ ምግብ ምን ማለት ነው?
3. ጤናማ ያልሆኑ ምግቦችን መመገብ ምን ችግር ያስከትላል?
4. ምግቦችን ሳይበላሹ የምናቆይባቸው ዘዴዎችን ዘርዝሩ::

ሐ. ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ ውስጥ የጤናማና ጤናማ ያልሆኑ ምግቦች ባህርያትን መሰረት በማድረግ አላቸው ወይም የላቸውም በማለት ሙሉ::

| ባህርያት | ልዩነታቸው | |
|---|---|---|
| | ጤናማ ምግቦች | ጤናማ ያልሆኑ ምግቦች |
| ያልተለመደ ሽታ | | |
| ያልተለመደ ጣዕም | | |
| ለእይታ የተለየ መልክ | | |

## 2.2. የምግብ ጠቀሜታ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች! ይህንን ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡

ምግቦችን በአራት ዋና ዋና ምድቦች ትከፍላላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃል**

- የምግብ ምድቦች



ሥዕል 3. የተለያዩ የምግብ አይነቶች

የቡድን ውይይት 1

ዓላማ፡ የምግብ ዓይነቶችን ምድብ መለየት

መመሪያ፡- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት ከዚህ በታች በተሰጡት ጥያቄዎች መሰረት በመወያየት በክፍላችሁ ውስጥ አቅርቡ፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን የምግብ አይነቶች በወረቀት ላይ ዘርዝሩ፡፡
2. የዘረዘራችኋቸውን የምግብ አይነቶች በአራቱ ዋና ዋና የምግብ ምድቦች መድቧቸው፡፡

ተማሪዎች! የምንመገባቸው ምግቦች በአራት የምግብ ምድቦች ይከፈላሉ። እነሱም፡-

1. አትክልትና ፍራፍሬዎች
2. እህልና ጥራጥሬዎች
3. ሥጋ
4. ወተትና የወተት ውጤቶች ናቸው።

ተማሪዎች! ጤንነታችንን ለመጠበቅ ጤናማ ምግቦችንና የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ይኖርብናል። አራቱ የምግብ ምድቦች ለሰውነታችን የተለያዩ ጥቅሞችን ይሰጣሉ።

## 1. አትክልትና ፍራፍሬዎች



ሥዕል 4. አትክልትና ፍራፍሬዎች

ሌሎች በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን አትክልትና ፍራፍሬዎች በመዘርዘር ጥቅማቸውን በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

## 2. እህልና ጥራጥሬዎች



ሥዕል 5. እህልና ጥራጥሬዎች

ሌሎች በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን እህልና ጥራጥሬዎች በመዘርዘር ጥቅማቸውን በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

## 3. ሥጋ



ሥዕል 6. የሥጋ ዓይነቶች

## 4. ወተትና የወተት ውጤቶች



ሥዕል 7. ወተትና የወተት ውጤቶች

| ተ.ቁ | የምግብ ምድቦች | ጥቅማቸው |
|---|---|---|
| 1 | አትክልትና ፍራፍሬዎች | በሽታን መከላከል |
| 2 | እህልና ጥራጥሬዎች | ጉልበትና ሙቀት መስጠት |
| 3 | ሥጋ | ሰውነትን ለመገንባትና ለመጠገን |
| 4 | ወተትና የወተት ውጤቶች | ጉልበት መስጠት ፣ በሽታን መከላከል ፣ ለዕድገትም ይጠቅማሉ |

ሠንጠረዥ 1. የምግብ ምድቦችና ጥቅሞቻቸው

## መልመጃ 2.2.

**ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮችን በማንበብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ፣ ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. ምግብ በሽታን ለመከላከል አስፈላጊ ነው።
2. ሰውነታችን ጉልበት የሚያገኘው አትክልትና ፍራፍሬዎችን ስንመገብ ነው።
3. ወተት ለዕድገት ይጠቅማል።

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ።**

1. አትክልትና ፍራፍሬዎችን መመገብ ለምን ይጠቅማል?

2. ሥጋ ምን አይነት ጥቅም ይሰጣል?
3. አራቱን የምግብ ምድቦች ዘርዝሩ።
4. እናንተ አዘውትራችሁ የምትመገቡትን የእህልና ጥራጥሬዎች አይነቶች ዘርዝሩ።

## ሀ. የምግብ ብክለት መንስዔዎችና መከላከያዎች

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

የምግብ ብክለትን ለመከላከል የሚያስችሉ የንፅሕና አጠባበቅ መንገዶችን ትለያላችሁ።

**ቁልፍ ቃላት**
- ብክለት
- የምግብ ብክለት



ሥዕል 8.የምግብ ብክለት መንስዔዎች

የቡድን ውይይት 2

ዓላማ፡- የምግብ መበከል ዋነኛ መንስዔዎችና መከላከያ መንገዶችን መለየት

መመሪያ፡- ቡድን በመመስረት ከዚህ በታች በተሰጡት ጥያቄዎች መሰረት በመወያየት በክፍላችሁ ውስጥ አቅርቡ፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች፡-

1. የምግብ መበከል ዋነኛ መንስዔዎችን ዘርዝሩ፡፡
2. የምግብ እንዳይበከል የምንጠቀምበትን ዘዴ ግለጹ፡፡

ብክለት ማለት በአንድ አካባቢ በሚገኙ ሀብቶች ውስጥ ጎጂ ነገር መግባት ነው፡፡ ስለዚህ የምግብ ብክለት ማለት ምግብ ጎጂ በሆኑ በአይን በማይታዩ ጥቃቅን ተህዋሲያን መበከል ነው፡፡



ሥዕል 9.የምግብ ብክለት መከላከያ ዘዴዎች

ተማሪዎች! ከሥዕሉ ምን ተማራችሁ?

የምግብ ብክለት መከላከያ ዘዴዎች፡- እጅን በሳሙና መታጠብ፣ ምግብን መክደን፣ የምግብ ማዘጋጃ ቦታን ማፅዳት፣ የምግብ ዕቃዎችን በአግባቡ ማጠብ፣ ንፁህ ውሃን መጠቀም፣ ጥፍርን መቁረጥ፣ ፀጉርን መሸፈን፣ አትክልትና ፍራፍሬዎችን በደንብ ማጠብና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### መልመጃ 2.3.

ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮችን በማንበብ ትክክል ከሆነ "እውነት"፣ ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡

1. የምግብ ማስቀመጫ ዕቃ ነፍሳት በቀላሉ የሚገቡበት መሆን የለበትም፡፡
2. አትክልትና ፍራፍሬዎች በሽታ ተከላካይ ምግቦች ናቸው፡፡
3. ምግብና ጤና ምንም ዓይነት ግንኙነት የላቸውም፡፡
4. ምግብን በማድረቅ ሳይበላሽ ረዘም ላለ ጊዜ ማቆየት ይቻላል፡፡
5. ጎጂ ተባዮች እንዳያርፉበት ምግብን መሸፈን የምግብ ብክለት መንስኤ ነው፡፡

ለ. በ 'ሀ' ስር ለተዘረዘሩት የምግብ ምድቦች በ 'ለ' ስር ከተዘረዘሩት የምግብ ዓይነቶች ጋር በትክክል አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. እህልና ጥራጥሬ | ሀ. እርጎ፣ አይብ |
| 2. ሥጋ | ለ. ባቄላ፣ ጤፍ |
| 3. ወተትና የወተት ውጤቶች | ሐ. ጎመን፣ ማንጎ |
| 4. አትክልትና ፍራፍሬዎች | መ. ዓሣ |

## 2.3. የግል ንፅሕና አጠባበቅ

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- የንፅሕና መጠበቂያ መንገዶችን ትገልፃላችሁ፡፡

**ቁልፍቃላት**

- የግል ንፅሕና
- በሽታ
- የንፅሕና ጉድለት

የቡድን ውይይት 3

ዓላማ፦ ስለግል ንፅሕና አጠባበቅ መግለፅ

መመሪያ፦ በቡድን በመሆን ከታች በቀረቡት ጥያቄዎች መሠረት ተወያይታችሁ የየቡድናችሁን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ።

የመወያያ ጥያቄዎች፦

1. የግል ንፅሕናችንን እንዴት እንጠብቃለን።
2. ፊታችሁን እና እጃችሁን መቼ መታጠብ እንዳለባችሁ ለመምህራችሁ ግለፁ።
3. በሥዕል



ሥዕል 10. የግል ንፅሕና አጠባበቅ



ሥዕል 11. ሲስተር ደራሮ እና ተማሪ ዳባሳ

### ቃለ-መጠይቅ

የሚከተለውን ቃለ መጠይቅ በጥሞና አንብቡ። ቃለ መጠይቁ ዳባሳ በሚባለው የሦስተኛ ክፍል ተማሪ የቀረበ ነው። መላሿ ደግሞ ሲስተር ደራሮ የተባሉ ነርስ ናቸው። ተማሪ ዳባሳና ሲስተር ደራሮን የሚወክሉ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ወጥተው ቃለመጠይቁን ያድርጉ።

ዳባሳ፡- እንደምን ዋሉ ሲስተር

ሲስተር፦ እንደምን ዋልክ ሱራፌል

ዳባሳ፦ የግል ንፅህና ማለት ምን ማለት ነው?

ሲስተር፦ የግል ንጽሕና ማለት ዘወትር የሰውነታችንን፣ የፀጉራችንንና የምንለብሳቸውን ልብሶች ንጽሕና መጠበቅ ማለት ነው። እንዲሁም ጥርሳችንን መፋቅና ጥፍራችንን መቁረጥ ማለት ነው።

ዳባሳ፦ የግል ንፅህና መጠበቅ ለምን ይጠቅማል?

ሲስተር፦ የግል ንፅህና መጠበቅ ራስን ከበሽታ ለመከላከል ይጠቅማል።

ዳባሳ፦ በሽታ ማለት ምን ማለት ነው?

ሲስተር፦ በሽታ ማለት የሰውነታችን ጤንነት መጓደል ማለት ነው።

ዳባሳ፦ የአካል ጉዳተኝነት በሽታ ነውን?

ሲስተር፦ ለምን ይህን ጥያቄ ልጠይቀኝ ቻልክ?

ዳባሳ፦ የአካል ጉዳተኝነት በሽታ ነው ሲባል ሰምቼ ነው።

ሲስተር፡- የአካል ጉዳተኝነት በሽታ አይደለም። አካል ጉዳተኝነት ማለት በተፈጥሮ ወይም በአደጋ ሊከሰት የሚችል ጉዳት ነው። ሁሉም ሰው ላይ ሊከሰት ይችላል። አካል ጉዳተኞች ከማንኛውም ሰው ጋር እኩል መሆናቸውን ተረድተን ፍቅር ልንሰጣቸው ይገባል።

ዳባሳ፦ በንፅህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች የትኞቹ ናቸው ?

ሲስተር፡- በንፅህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች ኮሌራ፣ ተቅማጥ፣ወስፋትና የመሳሰሉት ናቸው።

ዳባሳ፦ ለጠየኩት ጥያቄ በቂ ምላሽ ስለሰጡኝ ከልብ አመሰግናለሁ።

ሲስተር፡- እኔም ስለጤና ጉዳይ የማስረዳት ኃላፊነቴን በመወጣቴና አንተን በመርዳቴ ደስ ይለኛል።

ከውይይቱ የተገኙ ጠቃሚ ምክሮች

የተሟላ ጤንነት እንዲኖረን ንጽህናችንን መጠበቅ ይኖርብናል። የግል ንጽህናችንን አለመጠበቅ ለተለያዩ በሽታዎች ይዳርጋል። በንፅህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች እንደ እከክ ፣ ወስፋት ፣ ኮሌራና የመሳሰሉት ናቸው። አካል ጉዳተኞችን ማገዝ መልካም ተግባር ነው። አካል ጉዳተኝነት በሽታ ወይም ሕመም ሳይሆን በተፈጥሮና በአደጋ ሊከሰት የሚችል ጉዳት ነው።

የቡድን ውይይት 4

ዓላማ፦ ስለግል ንፅሕና ጥቅም መግለፅ

መመሪያ፦ ስድስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት ከታች በተሰጡት የመወያያ ጥያቄዎች መሠረት ተወያይታችሁ መልሳችሁን በፅሑፍ በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

የመወያያ ጥያቄዎች፦

1. የግል ንፅሕናችንን መጠበቅ ለምን ይጠቅማል?
2. የግል ንፅሕናችንን ባንጠብቅ ምን ጉዳት ይደርስብናል?
3. የግል ንፅሕናችንን ባንጠብቅ በሌሎች ሰዎች ላይስ ምን ዓይነት ጉዳት ያስከትላል?

## ሀ. ንፅሕናን ለምን እንጠብቃለን?

### የግል ንፅሕና መጠበቅ

- ራሳችንን ከበሽታ ለመከላከል ይጠቅማል፡፡
- ንቁ፣ ደስተኛና ጤነኛ ሆኖ ለመገኘት ያስችላል፡፡
- ሥራችንን ከሌሎች ሰዎች ጋር በትጋት ለማከናወን ያስችላል፡፡

### የግል ንፅሕናን አለመጠበቅ

- ሰውነት መጥፎ ጠረን እንዲኖረው ያደርጋል፡፡
- ከሌሎች ሰዎች ጋር ተግባብቶ የመሥራት ሁኔታ ይቀንሳል፡፡
- ለተለያዩ በሽታዎች ያጋልጣል፡፡
- የተለያዩ ተባዮች በፀጉራችንና በልብሳችን ውስጥ እንዲፈጠሩ መንስዔ ይሆናል፡፡

## ለ. ንፅሕናችንን ባንጠብቅ በሌሎች ላይ ምን ጉዳት ያደርሳል?



ሥዕል 11.ንጽሕናን አለመጠበቅ በሌሎች ላይ የሚያደርሰው ጉዳት

የቡድን ውይይት 5

ዓላማ፡- ንፅሕናችንን ባንጠብቅ በሌሎች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት መለየት

መመሪያ፡-ተማሪዎች! በቡድን በመሆን በትምህርት ቤታችሁ በሚገኘው የጤና ክበብ በመሄድ ንፅሕናችንን ባንጠብቅ በሌሎች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት በመወያየትና በመረዳት መልሳችሁን በክፍል ውስጥ አቅርቡ

ንፅሕናችንን ባንጠብቅ በሌሎች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት፡- የቤተሰብ ስራ መፍታት፣ ለተጨማሪ ወጭ ይዳርጋል፣ ለበሽታ መተላለፍ ምክንያት ይሆናል።

ንፅሕናችንን ባለመጠበቃችን ምክንያት ሌሎች ሰዎች ለተለያዩ ችግሮች ይጋለጣሉ።

ለምሣሌ፦ ደስተኛ ሆነው ሊቀርቡን አይችሉም፤ አብረውን መቆየት አይችሉም፣ አብረዉን መጫወት ፣ መማር ፣ እና መመገብ አይፈልጉም።

## ሐ. በንፅሕና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች



ሥዕል 12. በንፅሕና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች

የቡድን ውይይት 6

ዓላማ፦ በንፅሕና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎችን መዘርዘር

መመሪያ፦ ተማሪዎች! አምስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ በንፅሕና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎችን በመዘርዘር ተወያይታችሁ መልሳችሁን በክፍላችሁ ውስጥ አቅርቡ።

በግል ንጽህና ጉድለት ከሚከሰቱ የተለያዩ በሽታዎች መካከል ጥቂቶቹ ኮሌራ ፣ ተቅማጥ፣ የወስፋት በሽታ ናቸው። የወስፋት በሽታ በአብዛኛው ህፃናትን ያጠቃል። ይህም የሆነበት ምክንያት ልጆች በተበከለ አፈር ሲጫወቱ በአፈር ውስጥ የወስፋት ትል እንቁላሎች በጥፍሮቻቸው ላይ ይጣበቃሉ። ልጆች እጃቸውን በሚገባ ካልታጠቡ እነዚህ ጥፍሮቻቸው ውስጥ የተጣበቁት እንቁላሎች በአፋቸው በኩል ወደ አንጀታቸው ይገባሉ። ኮሌራ አጣዳፊና ተዛማች የሆነ የተቅማጥና የትውከት በሽታ ነው።

### መ. ጤናማና ሕመምተኛ ሰዎችን ማነፃፀር



ሥዕል 13. ንፅሕናውን የጠበቀ ተማሪና ያልጠበቀ ተማሪ

የቡድን ውይይት 7

ዓላማ፦ ጤናማና ህመምተኛ ሰዎችን ማወዳደር

መመሪያ፦ አምስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ከዚህ በታች በሚገኘው ሠንጠረዥ ውስጥ ጤናማ የሆኑና የታመሙ ልጆችን በማነፃፀር ከተወያያችሁ በኋላ የቀረውን አሟሉ፡፡

| ጤናማ ልጆች | በሽተኛ ልጆች |
|---|---|
| ጤናማ ናቸው | ብዙውን ጊዜ ይታመማሉ |
| | |
| | |
| | |
| | |

## ሠ. ለታመሙ ሰዎች የምናደርገው ርህራሄና እንክብካቤ



ሥዕል 14. ለታመሙ ሰዎች የሚደረግ ርህራሄና እንክብካቤ

ተግባር 2

ጭውውት

ዓላማ፦ ለታመሙ ሰዎች የምናደርገው ርህራሄና እንክብካቤን ማግለፅ

መመሪያ፦ ተማሪዎች! 5-7 አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት በየአከባቢያችሁ ለታመሙ ሰዎች የምታደርጉትን ርህራሄና እንክብካቤ የሚገልፅ ጭውውት አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁን አቅርቡ።

## መልመጃ 2.4.

ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች በማንበብ ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. የግል ንፅህናን መጠበቅ ለጤናችን ጠቃሚ ነው።
2. የምግብ ብክለትን በተለያዩ መንገዶች መከላከል ይቻላል።
3. በዓይናችን የማይታዩ ጥቃቅን ተህዋሲያን ምግቦችን ይበክላሉ።
4. የምንመገባቸው ምግቦች በሦስት ምድቦች ይመደባሉ።

ለ. በ 'ሀ' ስር ያሉትን የምግብ ጥቅሞች በ 'ለ' ስር ከተቀመጡት መገለጫዎች ጋር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሰውነትን ለመገንባትና ለመጠገን ይረዳል። | ሀ. ማንጎ |
| 2. ለሰውነታችን ሀይልና ሙቀት ይሰጣል። | ለ. ስጋ |
| 3. ሰውነታችንን ከበሽታ ይከላከላል። | ሐ. በቆሎ |

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ።

1. የግል ንፅህናችንን ባንጠብቅ በሌሎች ሰዎች ላይ ምን ጉዳት ያደርሳል?
2. የንፅህና መጠበቂያ መንገዶችን ዘርዝሩ።
3. በጤነኛ እና በሕመምተኛ ሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት አብራሩ።

## 2.4. የቁስ አካል አካላዊ ለውጦች

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት


ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ ፦

- የጠጣር፣ የፈሳሽና የጋዝ ባሕሪያትን ፍቺዎች በመስጠት ትገልፃላችሁ።
- የቁስ አካላትን (የጠጣር፣ ፈሳሽና ጋዝ) የሁነት ለውጥን ትገልፃላችሁ።

**ቁልፍ ቃላት**

- የሁነቶች ለውጥ
- ጠጣር
- ፈሳሽ
- ጋዝ

ተማሪዎች! ሁለተኛ ክፍል ስለ ቁሶች አካላዊ ባሕሪያት ተምራችኋል። በዚህ ክፍል ደግሞ ስለቁስ አካል የሁነት ለውጦች ትማራላችሁ።



| ጠጣር (በረዶ) | ፈሳሽ (ዉሃ) | ጋዝ (የውሃ ትነት) |
|---|---|---|

ሥዕል 15. ሦስቱ ሁነቶች

የቡድን ውይይት 8

ዓላማ፦ በጠጣር ፣ በፈሳሽና በጋዝ መካከል ያለውን ልዩነት መለየት

መመሪያ፡- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ጠጣር ምንድን ነው?
2. ፈሳሽ ምንድን ነው?
3. ጋዝ ምንድን ነው?
4. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ጠጣር ነገሮችን ዘርዝሩ።
5. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ፈሳሽ ነገሮችን ዘርዝሩ።
6. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ጋዝ የሆኑ ቁሶችን ዘርዝሩ።

ቁስ አካል ማለት ማንኛውም ቦታ የሚይዝና መጠነ ቁስ ያለው ነገር ነው። ቁስ አካል በሦስት ሁነቶች ይከፈላል። እነርሱም፦ ጠጣር ፣ ፈሳሽና ጋዝ ይባላሉ።

ጠጣር ማለት ውስን የሆነ ቅርፅና ይዘት ያለው ቁስ አካል ነው። የቅንጣጢታቸው አቀማመጥ የተጠጋጋ ነው።

ለምሣሌ ብረት ፣ ድንጋይ ፣ ጠመኔና የመሳሰሉት ጠጣር ናቸው።




ሥዕል 16. የጠጣር ምሳሌዎች

ፈሳሽ ማለት ውስን የሆነ ይዘት ያለው ነገር ግን ውስን የሆነ ቅርፅ የሌለው ቁስ አካል ነው። የቅንጣጢታቸው አቀማመጥ ከጠጣር አንጻር የተራራቀ ነው። ለምሣሌ፦ ውሃ ፣ ዘይት፣ ወተትና የመሳሰሉት ፈሳሽ ናቸው።



ወተት



ዉሃ

ሥዕል 17. የፈሳሽ ምሳሌዎች

ጋዝ ማለት ውስን የሆነ ቅርፅም ሆነ ይዘት የሌለው ቁስ አካል ነው። የቅንጣጢታቸው አቀማመጥ ከጠጣርና ከፈሳሽ አንጻር የተራራቀ ነው። ለምሣሌ፦ እንፋሎት፣ አየር




ሥዕል 18. የጋዝ ምሳሌ

ተማሪዎች! በሙቀት ልዩነት ምክንያት ቁስ አካላት ከአንዱ ሁነት ወደ ሌላኛው ሁነት ሊቀያየሩ ይችላሉ። ለምሣሌ ውሃ በሦስቱ ሁነቶች ይገኛል። እነርሱም፦ በረዶ (ጠጣር)፣ ውሃ (ፈሳሽ) እና ተን (ጋዝ) ናቸው። ለምሳሌ፦ ውሃን በጣም ብናቀዘቅዘው በረዶ ይሆናል። በረዶውን ብናቀልጠው በቀላሉ ወደ ፈሳሽ ይለወጣል። ፈሳሽ ውሃን ብናፈላ ወደ እንፋሎት (ትነት) ይለወጣል።



ሥዕል 19. የውሃ መገኛ ሁነቶች

በሁለተኛ ክፍል ትምህርታችሁ የዘረዘራችኋቸውን የቁስ አካል ባሕርያትን ታስታውሳላችሁ? ያስታወሳችሁትን ለመምህራችሁ ግለፁ።

እነዚህም፡- ቀለም፣ መጠን፣ ቅርፅ፣ ሟሚነትና የመሳሰሉት ናቸው። በሦስቱ ሁነቶች ውስጥ የሚካሄደው ለውጥ አካላዊ ባህርያት ነው።

የቡድን ውይይት 9

ዓላማ፡ የቁስ አካል አካላዊ ባህርያትንና ትርጉማቸውን (ፍቻቸውን) በመጠቀም የጋዝ ፣ የጠጣር እና የፈሳሽ ልዩነቶችን መግለፅ።

መመሪያ፡ ተማሪዎች! 5 አባላት ያለው ቡድን በመመስረት የሦስቱን ሁነቶች ልዩነት ከዚህ በታች በተሰጠው ሠንጠረዥ ላይ ሞልታችሁ መልሳችሁን በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

| ሁነት | ባህርያት | | |
|---|---|---|---|
| | ቅርፅ | የቅንጣጢት አቀማመጥ | ይዘት |
| ጠጣር | | | |
| ፈሳሽ | | | |
| ጋዝ | | | |

ተግባር 3.

የግል ሥራ

ዓላማ፡ ውሃ በሦስቱ ሁነቶች እንደሚገኝና በሙቀት ልዩነት ከአንዱ ወደ ሌላኛው ሁነት እንደሚቀየር በተግባር ማረጋገጥ

መመሪያ፡ ተማሪዎች! እያንዳንዳችሁ በቤታችሁ ቤተሰቦቻችሁ እንዲያግዟችሁ በማድረግ ከታች የቀረበውን ተግባራዊ ክንውን ቅደም ተከተሉን ተከትላችሁ በተግባር በማከናወን ያገኛችሁትን ውጤት በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

የሚያስፈልጉ ቁሶች፡ በረዶ ፣ ምድጃ ፣ የውሃ መጣጃ (ብረት ድስት)

የአሠራር ቅደም ተከተል፡

1. በረዶውን ብረት ድስቱ ውስጥ በመጨመር ምድጃ ላይ ጣዱት። የተመለከታችሁትን በደብተራችሁ ላይ ፃፉ።
2. ውሃን ብረት ድስት ውስጥ በመጨመር ምድጃ ላይ አፍሉት ለተወሰኑ ደቂቃዎች ከጠበቃችሁ በኋላ ያያችሁትን ውጤት በደብተራችሁ ላይ ፃፉ።
3. ውሃን በበረዶ ማስቀመጫ በማድረግ ፍሪጅ ውስጥ አስቀምጡ። ከቆይታ በኋላ ያያችሁትን ውጤት በደብተራችሁ ላይ ፃፉ።

ተማሪዎች! ከተግባራዊ ክንውናችሁ የተረዳችሁትን ለመምህራችሁ አቅርቡ።

- ፈሳሽ ወደ ጋዝ የሚለወጥበት ሂደት ትነት ይባላል።
- ጠጣር ወደ ፈሳሽ የሚለወጥበት ሂደት ቅልጠት ይባላል።
- ፈሳሽ ወደ ጠጣር የሚለወጥበት ሂደት ብርደት ይባላል።

## መልመጃ 2.5

ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች በማንበብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ስህተት ከሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. ውሃ ሲፈላ ወደ በረዶነት ይቀየራል።
2. ሙቀት ለሁነት ለውጥ ምክንያት ነው።
3. ጋዝ ውስን የሆነ ቅርፅ እና ይዘት አለው።
4. ቦታ የሚይዝና መጠነ ቁስ  ያለው ነገር ቁስ አካል ይባላል።
5. እንፋሎት የጋዝ ቁስ አካል ምሣሌ ነው።

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ፡፡

1. በረዶ የሚቀልጠው ምን ሲሆን ነው?
2. ሦስቱን የውሃ ሁነቶች ፃፉ፡፡

## 2.5. የብርሃን ጠቀሜታ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ

- የብርሃን ጥቅሞችን ትዘረዝራላችሁ፡፡

ቁልፍ ቃላት

- ብርሃን
- የብርሃን ጥቅሞች









ሥዕል 20.የብርሃን ምንጮች

የቡድን ውይይት 10

ዓላማ፦ ስለብርሃን ምንጭ እና ጥቅም መግለፅ

መመሪያ፦ አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

የመወያያ ጥያቄዎች፦

1. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ የሚገኙ የብርሃን ምንጮችን ዘርዝሩ።
2. የብርሃን ጥቅሞችን ዘርዝሩ።

የብርሃን ምንጮች በሁለት ይከፈላሉ። እነርሱም በተፈጥሮ የሚገኙ የብርሃን ምንጮችና ሰው ሰራሽ የብርሃን ምንጮች ናቸው። የተፈጥሮ የብርሃን ምንጮች የምንላቸው ፀሐይ ፣ ጨረቃና ክዋክብት ናቸው።

የፀሐይ ብርሃን በነፃ የሚገኝ የጉልበት ምንጭ ነው። ከፀሀይ የሚገኘውን ጉልበት በመጠቀም ልዩ ልዩ ተግባራትን ማከናወን ይቻላል። ለምሣሌ ልብስን ለማድረቅ፣ ለማየት፣ ለእፅዋት፣ እድገት፣ ሰብልን ለማድረቅ፣ ብርሃንን ወደ ሙቀት ጉልበት በመቀየር ምግብን ለማብሰል፣ ወደ ኤሌክትሪክ ጉልበት በመቀየር ለተለያዩ ነገሮች መጠቀምና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል። ሰው ሰራሽ የብርሃን ምንጮች የምንላቸው በመብራት ላይ የሚገኝ አምፑል፣ ኩራዝ፣ ሻማ፣ እና የመሳሰሉት ናቸው። አንድ ነገርን በግልፅ ማየት የሚቻለው በብርሃን ወይስ በጨለማ ነው? መልሱን ለመምህራችሁ ተናገሩ።




ሥዕል 21. ብርሃንና ጨለማ

ብርሃን ከሌለ ነገሮችን ማየት አንችልም። ብርሃን ነገሮችን ለማየት ይጠቅማል።

በጨለማ ደግሞ ነገሮችን ማየት አንችልም።

እፅዋቶች ምግባቸውን እንዲያዘጋጁና ለዕድገታቸው ብርሃን ያስፈልጋቸዋል።




ሥዕል 22. የፀሀይ ብርሃን ያገኘ እፅዋትና የፀሀይ ብርሃን ያላገኘ እፅዋት

ተግባር 4

በግል የሚከናወን ተግባር

ዓላማ፡ የፀሐይ ብርሃን ጥቅምን እንዲያውቁ ማድረግ

መመሪያ፡- ተማሪዎች! እያንዳንዳችሁ ከዚህ በታች የቀረቡት ሙከራዎች በቤታችሁ በመተግበር ያገኛችሁትን ውጤት በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

የሚያስፈልጉ ቁሶች፡ ሁለት በጣሳ የተተከሉ  ችግኞች

የአሠራር ቅደም ተከተል፡

1. አንዱን ችግኝ የፀሀይ ብርሃን ያለው ስፍራ ማድረግና ለተወሰኑ ቀናት ማቆየት
2. ሁለተኛውን ችግኝ የፀሀይ ብርሃን የሌለው ስፍራ (ጨለማ) ስፍራ ማድረግና ለተወሰኑ ቀናት ማቆየት
3. በተመሳሳይ ሰዓት እኩል መጠን ያለው ውሃ ማጠጣትና ለተወሰኑ ቀናት የሁለቱን ችግኞች ልዩነትን በማስተዋል  ከሙከራው ያገኛችሁትን ውጤት በደብተራችሁ ላይ መዝግቡና በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

## መልመጃ 2.6.

ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች በማንበብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. የብርሃን ምንጮች በሁለት ይከፈላሉ።
2. የፀሐይ ብርሃን በነፃ የሚገኝ የጉልበት ምንጭ ነው።
3. ተክሎች ምግባቸውን ለማዘጋጀት የፀሐይ ብርሃን አይጠቀሙም።

ለ. በ 'ሀ' ስር ለተዘረዘሩት በ 'ለ' ስር ከተዘረዘሩት ጋር በትክክል አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ብርሃን አመንጪ ያልሆነ | ሀ. ፀሐይ |
| 2. የተፈጥሮ የብርሃን ምንጭ | ለ. ብርሃን |
| 3. ነገሮችን ለማየት አስፈላጊ ነው | ሐ. መስታወት |

## ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ

1. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ብርሃን የምናገኘው ከየቱ ነው?

   ሀ. ፀሐይ  ለ. የሚበራ ኩራዝ  ሐ. የሚበራ ሻማ  መ. ሁሉም

2. ከሚከተሉት ውስጥ ሰው ሠራሽ የብርሃን ምንጭ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ፀሐይ  ለ. ጨረቃ  ሐ. የሚበራ ባትሪ  መ. ኮከብ

3. የብርሃን ጥቅም የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. የጉልበት ምንጭ ይሆናል  ለ. ለዕፅዋት ዕድገት ይጠቅማል

   ሐ. ለማየት ይጠቅማል  መ. ሁሉም መልስ ናቸው

### ማጠቃለያ

- ❖ ምግብና ጤና ተያያዥነት ስላላቸው ምግብን በጥንቃቄ መያዝና ማዘጋጀት አለብን።
- ❖ ምግብ በተለያዩ ነገሮች ይበከላል። በዐይናችን በማይታዩ ጥቃቅን ተህዋስያን ምግብ ስለሚበከል በጥንቃቄ መያዝ አለብን።
- ❖ ምግቦች ሳይበላሹ ረዘም ላለ ጊዜ ለማቆየት ማድረቅ፣ በጨው ማሸት እና በማቀዝቀዣ ውስጥ ማቆየት ያስፈልጋል።
- ❖ ምግቦች በአራት ምድቦች ይከፈላሉ። እነዚህም አትክልትና ፍራፍሬዎች፣ እህልና ጥራጥሬዎች፣ ሥጋ እና ወተትና የወተት ውጤቶች ናቸው።
- ❖ አራቱ የምግብ ምድቦች የተለያዩ ጥቅሞችን ለሰውነታችን ይሰጣሉ።የምግብ መበከል የተለያዩ በሽታዎችን ሊያስከትል ይችላል። በተለይም ኮሌራ፣ ተቅማጥና ወስፋት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።
- ❖ ንፅሕናን መጠበቅ ለጤናችን ወሳኝ ነው።
- ❖ ለታመሙ ሰዎች ርህራሄ እና እንክብካቤ ማድረግ ተገቢ ነው።
- ❖ ቁስአካል ቦታ የሚይዝና መጠነ ቁስ ያለው ነገር ነው።

- ❖ ቁስ አካል በሦስት ሁነቶች ይከፈላሉ። እነርሱም ጠጣር፣ ፈሳሽና ጋዝ ናቸው።
- ❖ የቁስ አካል የሁነት ለውጥ ሂደቶች የምንላቸው ትነት፣ ቅልጠት፣ ብርደትና የመሳሰሉት ናቸው።
- ❖ የብርሃን ምንጮች ሁለት ናቸው። እነርሱም ሰው ሰራሽ የብርሃን ምንጮችና ተፈጥሮአዊ የብርሃን ምንጮች ናቸው።
- ❖ ብርሃን ለማየት፣ ለእፅዋት ምግባቸውን እንዲያዘጋጁ፣ለዕፅዋት ዕድገት እና ለጉልበት ምንጭነት ይጠቅማል።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች በማንበብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. ለታመሙ ሰዎች ርህራሄና እንክብካቤ ማድረግ ተገቢ ነው።
2. አተር፣ ገብስና ጤፍ የአትክልትና ፍራፍሬ የምግብ ምድቦች ናቸው።
3. ምግብን በንፅሕና አለማዘጋጀት ለምግብ ብክለት ያጋልጣል።
4. ፈሳሽን ወደ ጋዝ የመለወጥ ሂደት ቅልጠት ይባላል።
5. ብርሃን አንዱ የጉልበት ምንጭ ነው።

**ለ. በ 'ሀ' ስር ለተዘረዘሩት የሁነት ለውጥ ሂደቶች ከ 'ለ' ስር ከተዘረዘሩት አማራጮች ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ፈሳሽ ወደ ጠጣር የመለወጥ ሂደት | ሀ. ቅልጠት |
| 2. ጠጣር ወደ ፈሳሽነት የመለወጥ ሂደት | ለ. ብርደት |
| 3. ፈሳሽን ወደ ጋዝ የመለወጥ ሂደት | ሐ. ትነት |

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።**

1. እንፋሎት ከሚከተሉት ውስጥ በየትኛው ይመደባል?

ሀ. ጠጣር ለ. ፈሳሽ ሐ. ጋዝ

2. ከሚከተሉት ውስጥ ጠጣር የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ዳቦ ለ. ፈሳሽ ዘይት ሐ. ውሃ መ. አልኮል

3. የብርሃን ጥቅም ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. የጉልበት ምንጭ ሐ. ለመስማት

ለ. ለማየት መ. ለማድረቅ

4. ከአራቱ የምግብ ምድቦች የማይመደበው የቱ ነው?

ሀ. ሲጋራ ለ. ጥራጥሬ ሐ. ወተት መ. ፍራፍሬ

5. ስለ ሕመምተኛ ሰው ትክክል ያልሆነው ዐረፍተ ነገር የቱ ነው?

ሀ. ሥራውን በአግባቡ ማከናወን አይችልም

ለ. ደስተኛ አይደለም

ሐ. ርህራሄና እንክብካቤ አይፈልግም

መ. ለሕክምና የሚውል ተጨማሪ ገንዘብ ያስፈልገዋል

መ. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተገቢው መልስ ሙሉ።

1. በምግብ ብክለት አማካኝነት የሚከሰቱ በሽታዎች---------፣----------እና-------- ናቸው።
2. አራቱ የምግብ ምድቦች ---------፣---------፣-----------እና-------------ናቸው።
3. የብርሃን ምንጮች--------------እና--------------ናቸው።

## ፍተሻ

ልታከናውኗቸው የምትችሏቸውን ተግባራት በመለየት በእያንዳንዱ ሳጥን ውስጥ ይህንን (✓) ምልክት አስቀምጡ።

1. ጤናማ ምግቦችና መጠጦችን መለየት እችላለሁ። ☐
2. ምግቦችን በአራት መሠረታዊ ምድቦች መክፈል እችላለሁ። ☐
3. የምግብ ብክለትን ለመከላከል የሚያስችሉ የንጽሕና አጠባበቅ መንገዶችን እለያለሁ። ☐
4. የንፅህና መጠበቂያ መንገዶችን እለያለሁ። ☐
5. የጠጣር፣ ፈሳሽና ጋዞች ባሕርያትን ፍችዎች መስጠትና መግለጽ እችላለሁ። ☐
6. የቁስ አካላትን (የጠጣር፣ የፈሳሽና የጋዞች) የሁነት ለውጥ መግለጽ እችላለሁ። ☐
7. የብርሃንን ጥቅሞች መዘርዘር እችላለሁ። ☐

# ምዕራፍ ሦስት

# ተፈጥሮአዊ አካባቢ

### ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት ልዩነቶችን ትገልጻላችሁ፡፡
- በተለያዩ ወቅቶች የሚጠበቁ የአየር ሁኔታዎችን ትገልጻላችሁ፡፡
- በወረዳችሁ የሚኖረውን የሙቀት መጠን ልዩነት ትገመግማላችሁ፡፡
- በወረዳችሁ የሚኖረውን የዝናብ መጠን ሥርጭት ታወዳድራላችሁ፡፡
- በወረዳችሁ የአየር ንብረትን የሚቆጣጠሩ ነገሮች (ከፍታ፣ የደን ሽፋንና ከባህር ያለው ርቀት) ትለያላችሁ፡፡
- የተፈጥሮና የሰው ሠራሽ ሀብቶችን ምንነት ትገልጻላችሁ፡፡
- በወረዳችሁ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን ትለያላችሁ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብቶችን ጥቅም ትገልጻላችሁ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ምንነትን ትገልጻላችሁ፡፡
- በወረዳችሁ የሚስተዋሉ ዋናዋና የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንሥኤዎችንና ውጤቶችን ትገልጻላችሁ፡፡

- በወረዳችሁ የሚዘወተሩ ሀገር በቀልና የተለመዱ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የእንክብካቤ ዘዴዎችን ትገልጻላችሁ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ለቀጣይ ትውልድ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ዋጋ ትሰጣላችሁ፡፡
- ብክለትን ለመቀነስ የሚያግዙ የመፍትሔ ሀሳቦችን ታቀርባላችሁ፡፡
- በትምህርት ቤታችሁና በቀበሌያችሁ መልሶና ደጋግሞ የመጠቀም ዘዴዎችን ታዘወትራላችሁ፡፡
- ቆሻሻን ያለአግባብ ማስወገድ በአካባቢያቸሁ ላይ የሚያመጣውን ተፅዕኖ ትገልጻላችሁ፡፡
- ንጽሕናው የተጠበቀ አካባቢ የሚሰጠውን ጠቀሜታ በተመለከተ ሐሳብ ትሰጣላችሁ፡፡

የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች

3.1. የወረዳችን አየር ንብረት

3.2. የተፈጥሮ ሀብቶች

3.3. የተፈጥሮ ሀብቶች ለወረዳችሁ ህልውናና ዕድገት ያለው ፋይዳ

3.4. በትምህርት ቤት እና በቀበሌያችሁ የሚስተዋሉ ተገቢ እና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች

3.5. ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ተፅዕኖዎች

## መግቢያ

የተፈጥሮ አከባቢያችን ሕይወት ያላቸውና ሕይወት የሌላቸውን ነገሮች ይይዛል። ሕይወት ያላቸው ነገሮች እፅዋትና እንሰሳት ናቸው። ሕይወት የሌላቸው ነገሮች አየር፣ አፈር፣ ውሃ፣ ማዕድናት ናቸው። የሰው ልጅ ሕይወት ያላቸውና ሕይወት የሌላቸውን ነገሮች መሠረታዊ ፍላጎቱን ለማሟላት ይጠቀምባቸዋል።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ወረዳችሁ የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት፣ የተፈጥሮ እና ሰው ሠራሽ ሐብቶች፣ የተፈጥሮ ሐብቶች ለወረዳችሁ ሕልውናና ዕድገት ስላላቸው ፋይዳ በትምህርት ቤት እና በቀበሌያችሁ የሚስተዋሉ ተገቢና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች እና ተገቢ ያልሆነ የቆሻሻ አወጋገድ ተፅዕኖዎች ትማራላችሁ። ስለዚህ የተፈጥሮ ሐብቶችን በጥንቃቄና በብልሐት ጥቅም ላይ ማዋል ይጠበቅብናል።

## 3.1. የወረዳችን አየር ንብረት

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት ልዩነቶችን ትገልጻላችሁ።
- በተለያዩ ወቅቶች የሚጠበቁ የአየር ሁኔታዎችን ትገልጻላችሁ።
- በወረዳችሁ የሚኖረውን የሙቀት መጠን ልዩነት ትገመግማላችሁ።
- በወረዳችሁ የሚኖረውን የዝናብ መጠን ስርጭት ታወዳድራላችሁ።
- በወረዳችሁ የአየር ንብረትን የሚቆጣጠሩ ነገሮችን ትለያላችሁ።

**ቁልፍ ቃላት**

- የአየር ሁኔታ
- የአየር ንብረት
- የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች



*ሥዕል 1 የተለያዩ የአየር ሁኔታዎች*

**የቡድን ውይይት 1**

ዓላማ :-የአየር ሁኔታና የአየር ንብረትን መለየት

መመሪያ፡- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን በደብተራችሁ ላይ ፃፉ፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

1. የአየር ሁኔታ ምንድን ነው ?
2. የአየር ንብረት ምንድን ነው ?
3. በአየር ሁኔታና በአየር ንብረት መካከል ያለውን ልዩነትና ዝምድና ፃፉ፡፡

የአየር ሁኔታ ማለት በአንድ አካባቢ ከጊዜና ከቦታ አንፃር በየጊዜው የሚለዋወጥ የአየር ባህርይ ነው:: ዋና ዋና የአየር ሁኔታ መገለጫዎች የሚባሉት ሞቃታማ፣ ቀዝቃዛማ፣ ዝናባማ፣ ደመናማ፣ ውርጫማና የመሳሰሉት ናቸው::

የአየር ንብረት ማለት በአንድ አካባቢ ረዘም ላለ ጊዜ የሚታይ አማካይ የአየር ሁኔታ ነው::

የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት ያላቸው ዝምድና ሁለቱም የአንድን አካባቢ የአየር ባህርይ ይገልፃሉ:: የአየር ሁኔታ ለአየር ንብረት ውጤት መነሻ ነው:: ስለዚህ የአየር ሁኔታ ከሌለ የአየር ነብረት ውጤትን ማወቅ አይቻልም::

የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት ያላቸው ልዩነት የአየር ሁኔታ ከጊዜና ከቦታ አኳያ በየቀኑ የሚለዋወጥ የአየር ባህርይ ሲሆን የአየር ንብረት ደግሞ ረዘም ላለ ጊዜ የሚታይ አማካይ የአየር ሁኔታ ውጤት ነው::

ወቅቶች በአራት ይከፈላሉ:: እነርሱም:-መኸር፣ በጋ፣ በልግና ክረምት ናቸው:: እነዚህ ወቅቶች የራሳቸው የሆነ የተለያየ የአየር ሁኔታ አላቸው::

| ተ.ቁ | ወቅቶች | የአየርሁኔታ |
|---|---|---|
| 1 | መኸር | ቀዝቃዛማ፣ ንፋሳማ |
| 2 | በጋ | ደረቃማ፣ ፀሀያማ (ሞቃታማ) |
| 3 | በልግ | ከፊል ዝናባማ፣ ከፊል ደመናማ |
| 4 | ክረምት | ዝናባማ፣ ደመናማ፣ ቀዝቃዛ |

ሠንጠረዥ 3.1 አራቱ ዋና ዋና ወቅቶች

ተግባር 1

ዓላማ፡ በወረዳችሁ የሙቀት መጠንና የዝናብ ስርጭት መገምገምና ማወዳደር

መመሪያ፡- በየግላችሁ የወረዳችሁን የአየር ሁኔታ ለአንድ ሣምንት ከተከታተላችሁ በኋላ በየቀኑ ያገኛችሁትን ውጤት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

ተግባር 2

ዓላማ፡ በወረዳችሁ የአየር ንብረትን የሚቆጣጠሩ ነገሮች መለየት

መመሪያ፡- የወረዳችሁን የደን ሽፋን እና ከፍታ በመመልከት ከአየር ንብረት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ገምግማችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች የሚባሉት ሙቀትና ቅዝቃዜ፣ የአየር ግፊት፣ እርጥበት፣ ንፋስ፣ የፀሐይ ጨረርና የዝናብ ስርጭት ናቸው፡፡

የአየር ንብረት የሰው ልጅ የዘወትር እንቅስቃሴን ሊወስን የሚችል ተፈጥሮአዊ ክስተት ነው፡፡ ለምሳሌ፡ የእርሻ ሥራን፣ የከብት እርባታን፣ የዕፅዋት ዕድገትን፣ የአኗኗር ዘይቤን የመሳሰሉት ላይ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ አለው፡፡

## መልመጃ 3.1

ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች በማንበብ ትክክል ከሆነ “እውነት” ትክክል ካልሆነ “ሐሰት” በማለት መልሱ፡፡

1. የወረዳዎች የአየር ሁኔታ ተመሳሳይ ነው፡፡
2. የአየር ሁኔታ ከጊዜና ከቦታ አንፃር በየጊዜው ይለዋወጣል፡፡
3. ሙቀት አንዱ የአየር ንብረት ተቆጣጣሪ ነው፡፡

ለ. በ ‘ሀ’ ስር ለተቀመጡት ወቅቶች በ ‘ለ’ ስር ካሉት የወቅቶች የአየር ሁኔታ ጋር አዛምዱ፡፡

| | ሀ | ለ |
|---|---|---|
| 1. | ክረምት | ሀ. ንፋሳማ |
| 2. | መኸር | ለ. ዝናባማ |
| 3. | በጋ | ሐ. ከፊል ዝናባማ |
| 4. | በልግ | መ. ደረቃማ |

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎችን ዘርዝሩ፡፡
2. የአየር ሁኔታ መገለጫዎችን ጻፉ፡፡

## 3.2. የተፈጥሮ ሀብቶች

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ሀብቶችን ምንነት ትገልጻላችሁ፡፡
- በወረዳችሁ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን ትለያላችሁ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብቶችን ጥቅም ትገልጻላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- የተፈጥሮ ሀብት
- ሰው ሰራሽ ሀብት

ተማሪዎች! የምታውቋቸውን የተፈጥሮ ሀብቶችና ሰው ሰራሽ ሀብቶች ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡



ሥዕል 4 ተፈጥሮአዊ ሀብቶች እና ሰው ሠራሽ ሀብቶች

**የቡድን ውይይት 2**

ዓላማ፡- ስለተፈጥሮ ሀብቶችና ሰው ሰራሽ ሀብቶች ምንነት መግለፅ

መመሪያ፡- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን በደብተራችሁ ላይ ፅፋችሁ በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

1. የተፈጥሮ ሀብት ምንድን ነው?
2. ሰው ሰራሽ ሀብት ማለት ምን ማለት ነው?
3. የተፈጥሮ ሀብቶችና ሰው ሰራሽ ሀብቶች ያላቸውን ዝምድና ግለፁ፡፡

የተፈጥሮ ሀብቶች የሚባሉት በተፈጥሮ የምናገኛቸውና ለሰው ልጆች ጥቅም የሚውሉ ናቸው። አፈር፣ አየር፣ ውሃ፣ የዱር እንስሳት፣ አፅዋትና የመሳሰሉት በሲዳማ ክልል ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸው። የተፈጥሮ ሀብቶቻችን ጉዳት እንዳይደርስባቸው መንከባከብና ጥቅም ላይ ማዋል አለብን።

ሰው ሰራሽ ሀብቶች የሰው ልጅ ዕውቀቱን፣ጥበቡንና ሀብቱን በመጠቀም የሰራቸው ሀብቶች ናቸው። ሐውልቶች፣ ቤተ-እምነቶች፣ ቤተ-መንግሥት፣ ድልድዮች፣ አደባባዮች፣ መንገዶችና የመሳሰሉት በሲዳማ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሰው ሠራሽ ሀብቶች ናቸው።

የተፈጥሮ ሀብቶችና ሰው ሠራሽ ሀብቶች እርስ በርሳቸው ግንኙነት አላቸው። ሰው ሠራሽ ሀብቶች ለመሥራት የሰው ልጅ የተፈጥሮ ሀብቶችን ይጠቀማል።

ለምሳሌ:- ሐውልቶችን፣ መንገዶችን፣ ቤተ-እምነቶችን፣ ቤተ-መንግስትን፣ ድልድዮችንና የመሳሰሉትን ለመገንባት አፈር፣ ውሃ፣ አፅዋት፣ አየር ይጠቀማሉ።

የቡድን ውይይት 3


ዓላማ:- በወረዳችሁ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን መለየትና ጥቅማቸውን መዘርዘር

መመሪያ፡- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የተፈጥሮ ሀብቶችን ጥቅም ከታች በተቀመጠው ሠንጠረዥ ውስጥ ፃፉ።

| የተፈጥሮ ሀብቶች | ጥቅሞቻቸው |
|---|---|
| ውሃ | |
| አፈር | |
| አየር | |
| እፅዋት | |
| የዱር እንስሳት | |

## ሀ. የአፈር ጥቅም

አፈር ከተፈጥሮ ሀብቶች አንዱ ነው። አፈር በመሬት ገፅ ላይ የሚታይ ከጥቃቅን የድንጋይ ስብርባሪ፣ የእፅዋትና እንስሳት ብስባሽ የሚፈጠር የተፈጥሮ ሀብት ነው። አፈር ለእፅዋት እድገት፣ ለእርሻ ሥራ፣ ለሸክላ ሥራ፣ ለግንባታ ሥራ እና ለመሳሰሉት ይጠቅማል። አፈር ለሰው ልጆችና ለእፅዋት ከፍተኛ ጠቀሜታ ስላለው ልንንከባከበው ይገባል።





ሥዕል 5 የአፈር ጥቅም

## ለ. የእፅዋት ጥቅም

እፅዋት ለልዩ ልዩ አልባሳት መሥሪያነት ለምሳሌ፦ ጥጥ፣ መጠለያዎችን ለመገንባት ለምሳሌ፦ እንጨትና ሳር፣ ለምግብ ምንጭነት ለምሳሌ፦ አትክልትና ፍራፍሬዎች፣ እህልና ጥራጥሬ፣ አፈር እንዳይሸረሸር በሥራቸው ደግፈው ለመያዝ፣ የዱር እንስሳት እንዳይሰደዱ ለመጠለያነት፣ ከኤሌክትሪክ በተጨማሪ ምግብን ለማዘጋጀት ለጉልበት ምንጭነት ፣የተለያዩ መድኃኒቶችን ለመሥራትና ለመሳሰሉት ይጠቅማሉ።





ሥዕል 6 የእፅዋት ጥቅም

## ሐ. የውሃ ጥቅም

ውሃ በቤት ውስጥ፦ ምግብ ለማዘጋጀት፣ ለንፅሕና፣ ለመጠጥ አገልግሎት ይውላል።

ለግብርና፦ ለመስኖ አገልግሎት፣ ለእንስሳት መጠጥ ይጠቅማል።

ለኢንዱስትሪ፦ የማምረቻ መሣሪያዎችን ለማቀዝቀዝ፣ ቆሻሻን ለማስወገድ፣ ነገሮችን ለማሟሟት ይጠቅማል።

በተጨማሪም ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫነት ይጠቅማል።









ሥዕል 7 የውሃ ጥቅም

### መ. የዱር እንስሳት ጥቅም





ሥዕል 8 የዱር እንስሳት

የዱር እንስሳት ለገቢ ምንጭነት ይሆናሉ፡- የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጎብኚዎችን በመሳብ እና አርጅተው ሲሞቱ የአካል ክፍሎቻቸውን (ቆዳቸውን፣ቀንዳቸውን፣ጥርሳቸውን) የመሳሰሉትን በመሸጥ ገቢ ያስገኛሉ።

### ሠ. የአየር ጥቅም



ሥዕል 9 የአየር ጥቅም

አየር ለሰው ልጅ በአጠቃላይ ሕይወት ላላቸው ነገሮች አስፈላጊ ነው፡፡ አየር ለሰው ልጅ፣ ለእንስሳትና ለእፅዋት ለመተንፈስ ያገለግላል፡፡ እፅዋት ለእድገታቸው አየርን ይጠቀማሉ፡፡ በተጨማሪም አየር የመኪና ጎማን፣ ኳስን፣ ፊኛን በአየር ለመሙላት ይጠቅማል፡፡

## መልመጃ 3.2

**ሀ. በ ‘ሀ’ ስር ለተዘረዘሩት የተፈጥሮ ሀብቶች ጥቅም በ ‘ለ’ ስር ካሉት የተፈጥሮ ሀብቶች ጋር አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ለመጠጥ አገልግሎት ይውላሉ | ሀ. እፅዋት |
| 2. ለመተንፈስ ይጠቅማል | ለ. አየር |
| 3. አፈር እንዳይሸረሸር ይከላከላል | ሐ. አፈር |
| 4. ለሸክላ ሥራ ያገለግላል | መ. ውሃ |

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡**

1. የተፈጥሮ ሀብት ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ውሃ ለ. ሐውልት ሐ. አፈር መ. አየር

2. የእፅዋት ጥቅም የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. መድኃኒት ለመሥራት ለ. መጠለያ ለመገንባት

   ሐ. ለምግብነት መ. ሁሉም መልስ ናቸው

3. የአፈር ጥቅም ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ለግንባታ ሥራ ለ. ለምግብነት

   ሐ. ለእርሻ ሥራ መ. ለሸክላ ሥራ

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ።

1. በወረዳችሁ የሚገኙ ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ ሀብቶችን ዘርዝሩ።
2. የዱር እንስሳትን ጥቅም ፃፉ።

## 3.3 የተፈጥሮ ሀብቶች ለወረዳችሁ ህልውናና ዕድገት ያለው ፋይዳ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ምንነትን ትገልጻላችሁ።
- በወረዳችሁ የሚስተዋሉ ዋና ዋና የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን መንስኤዎችንና ውጤቶችን ትገልጻላችሁ።
- በወረዳችሁ የሚዘወተሩ ሀገር በቀልና የተለመዱ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የእንክብካቤ ዘዴዎችን ትገልጻላችሁ።

የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ለቀጣይ ትውልድ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ትገልጻላችሁ።

**ቁልፍ ቃላት**

- የተፈጥሮ ሀብት መመናመን
- የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ
- ሀገር በቀል

ሀ. የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ምንነት

የቡድን ውይይት 4

ዓላማ፦ የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን ምንነት መገለጽ

መሪያ፦ ተማሪዎች! አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት ከዚህ በታች በቀረው የመወያያ ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

1. የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግለጹ።







ሥዕል 10 የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን

❖ ተማሪዎች! ስዕሎቹን በመመልከት የተረዳችሁትን ሐሳብ ለመምህራችሁ ግለፁ።

የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ማለት በተፈጥሮ የሚገኙ ሀብቶች በመጠን እና በአይነት እየቀነሱ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው።

የተፈጥሮ ሀብቶች በአግባቡ ካልተያዙ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሱ በመሄድ በመጨረሻም ሊጠፉ ይችላሉ። ስለዚህ በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ በሚደርሰው የጉዳት መጠን የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን ይከሰታል።

## ለ. በወረዳችሁ የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንስኤዎችና ውጤቶች

ተማሪዎች! በወረዳችሁ የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንስኤዎች ምን ምን እንደሆኑ ታውቋቸዋላችሁ? ውጤቶቹስ?

ሥዕል 11 የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንስኤዎች

**የቡድን ውይይት 5**

**ዓላማ፡-** በወረዳችሁ የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን መንስኤዎችና ውጤቶችን መለየት

**መመሪያ፡-** ተማሪዎች! አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት ከዚህ በታች በቀረቡት የመወያያ ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በወረዳችሁ የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን መንስኤዎችን ዘርዝሩ፡፡
2. የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን ምን አይነት ውጤቶች ያስከትላል?

ተማሪዎች! ከውይይታችሁ እንደተረዳችሁት የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንስኤዎች ብዙ ናቸው፡፡

1. አርሶ አደሮች ሰፊ የእርሻ ቦታ ለማግኘት እፅዋትን ይጨፈጭፋሉ፡፡
2. ሰዎች የማገዶ እንጨት ለማግኘት እፅዋትን ይጨፈጭፋሉ፡፡
3. ለግንባታ ሥራ እፅዋትን በመቁረጥ አፈር እንዲሸረሸር ያደርጋል፡፡
4. ከፍተኛ ዝናብ በሚዘንብበት ወቅት አፈር በጎርፍ አማካኝነት ይሸሸረሸራል፡፡
5. የዱር እንስሳት ደኖች በሚጨፈጨፉበት ሰዓት ይሰደዳሉ፡፡

6. አየር ከኢንዱስተሪ፣ ከተሽከርካሪዎችና ቆሻሻ ሲቃጠል በሚወጡ ጭሶች ይበከላል።

የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን የሚያስከትለው ውጤት፡- የአየር መበከል፣ጎርፍ፣ የሙቀት መጨመር፣ የበሽታ መስፋፋት፣ ረሃብና ድርቅ የመሳሰሉት ናቸው።

## ሐ. በወረዳችሁ የሚዘወተሩ ሀገር በቀልና የተለመዱ የተፈጥሮ ሀብቶች ጥበቃና እንክብካቤ ዘዴዎች





ሥዕል 12 የተፈጥሮ ሀብት አጠባበቅ ዘዴዎች

የቡድን ውይይት 6

ዓላማ፦ በወረዳችሁ የሚዘወተሩ ሀገር በቀልና የተለመዱ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ዘዴዎች መግለፅ

መመሪያ፡- አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት ከዚህ በታች በቀረበው የመወያያ ጥያቄ ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅረቡ፡፡

የመወያያ ጥያቄ

1. የተፈጥሮ ሀብት ጉዳቶችን ለመቀነስ በወረዳችሁ የሚዘወተሩ ሀገር በቀልና የተለመዱ የተፈጥሮ ሀብቶች ጥበቃና እንክብካቤ ዘዴዎችን በዝርዝር ግለፁ፡፡

ሀገር በቀል የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ማለት በአንድ ሀገር ውስጥ ያሉ ህዝቦች ከጥንት ጀምሮ የራሳቸውን እውቀት ተጠቅመው የተፈጥሮ ሀብትን የሚንከባከቡበት ዘዴ ነው፡፡ በወረዳችሁ የሚዘወተሩ ሀገር በቀልና የተለመዱ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ ዘዴዎች አሉ፡፡ እነዚህም፡-

የእንስሳት ፅዳጅ /ፍግ/፡- የአፈርን ለምነት ለመጨመር ይጠቅማል፡፡

ዛፍ መትከል፡- የአፈር መሸርሸርን፣ የአየር ብክለትን ይከላከላል፡፡

- የዱር እንሰሳት እንዳይሰደዱ ለመጠበቅ ይረዳል፡፡
- የአካባቢን ውበት ለመጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡

አዝዕርትን አፈራርቆ መዝራት፡- አዝዕርቶች በየጊዜው እየተፈራረቁ በሚዘሩበት ወቅት የአፈር ለምነት ይጨምራል፡፡

እርከን መሥራት፡- አፈር በቀላሉ በጎረፍ እንዳይሸረሸርና ለምነቱን ጠብቆ እንዲቆይ ይረዳል፡፡

አግድም ማረስ፡- አፈር በቀላሉ በውሃ እንዳይሸረሸርና ለምነቱን ጠብቆ እንዲቆይ ይረዳል፡፡

### የአፈር አጠባበቅ ዘዴዎች

አፈር እንዳይሸረሸር የሚረዱ የመከላከያ ዘዴዎች፦ ዛፍ መትከል፣ የዕፅዋት መቃጠልን መከላከል፣ እርከን መሥራት፣ የግጦሽ መሬትን ከመጠን በላይ አለማስጋጥ አፈር በጎርፍና በንፋስ አማካኝነት እንዳይሸረሸር የሚረዱ ናቸው፡፡

## የዕፅዋት አጠባበቅ ዘዴዎች

> የቡድን ውይይት 7
>
> ዓላማ፡ የዕፅዋት አጠባበቅ ዘዴዎችን ማብራራት
>
> መመሪያ፡ ተማሪዎች! አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የዕፅዋት መጨፍጨፍን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅረቡ፡፡

የዕፅዋት ጥበቃ ማለት ዛፎችን ያለበቂ ምክንያት አለመቁረጥ፣ አለመጨፍጨፍ እና አለማቃጠል ነው፡፡

የዕፅዋት ውድመትን ለመከላከል የሚጠቅሙ ዘዴዎች፡- ማንኛውንም ዛፍ ያለበቂ ምክንያት አለመቁረጥ፣ እፅዋቶች እንዳይቃጠሉ ጥናቃቄ ማድረግ፣ ለአገልግሎት በተቆረጡ ዛፎች ምትክ ብዙ የዛፍ ችግኞችን መትከልና መንከባከብ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የእፅዋት መትከል አስፈላጊነት፡- የአየር ብክለትን ለመቀነስ፣ የአፈር ለምነትን ለመጠበቅ፣ አካባቢን ለማስዋብ፣ መገልገያ እቃዎችን ለመስራትና ለመሳሰሉት ያስፈልጋል፡፡

> ተግባር 3
>
> ዓላማ፡ የእፅዋት መትከልን አስፈላጊነት በተግባር ማየት
>
> መመሪያ፡- ተማሪዎች! ሰባት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ በትምህርት ቤታችሁ ግቢ ውስጥ የእፅዋት መትከያ ቦታ አዘጋጅታችሁ ችግኝ በመትከልና በመንከባከብ የሚሰጡትን ጥቅም ለሌሎች አስረዱ፡፡

የተፈጥሮ ሀብቶችን መንከባከብ ለቀጣይ ትውልድ የሚሰጠው ጥቅም፡- ቀጣዩ ትውልድ መሰረታዊ ፍላጎቶቹን ማለትም መጠለያቸውን፣ ምግባቸውን፣ ልብሳቸውንና

የሚያከናውኗቸውን ስራዎች በቀላሉ ለማሟላት ይጠቅማቸዋል፡፡ ሀገራቸው ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ጎብኚዎች ተስማሚ እንድትሆን ያደርጋል፡፡ ቀጣዩ ትውልድ ምቹ የሆነ አካባቢ እንዲያገኝና ደስተኛ ሆኖ እንዲኖር ይረዳዋል፡፡ በመሆኑም ቀጣዩ ትውልድ የተፈጥሮ ሀብቶችን እንዲከባከብ ትልቅ ኃላፊነት የተሰጠው መሆኑን መረዳት ይኖርበታል፡፡

## መልመጃ 3.3

ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች በማንበብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡

1. የእፅዋት መመናመን የዱር እንስሳት እንዲሰደዱ ያደርጋል፡፡
2. የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቅ ለቀጣይ ትውልድ ጠቃሚ ነው፡፡
3. የተፈጥሮ ሀብቶች የእርስ በርስ ግንኙነት አላቸው፡፡
4. እርከን መሥራት አገር በቀል የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ዘዴ ነው፡፡
5. ዛፍ መትከል ለአፈር መሸርሸር መንስኤ ነው፡፡

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡

1. ሀገር በቀል እና የተፍጥሮ ሀብት እንክብካቤ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. አግድም ማረስ　　ለ. እርከን መሥራት

   ሐ. የእንስሳት ፅዳጅ መጠቀም　　መ. ሁሉም መልስ ናቸው

2. የእፅዋት ጥበቃ ዘዴ ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ዛፍ መትከል　　ለ. ዛፍ ማቃጠል　　ሐ. ዛፍን መንከባከብ

3. አግድም ማረስ የየትኛው የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ዘዴ ነው?

   ሀ. የዱር እንስሳት　　ለ. የአፈር　　ሐ. የአየር　　መ. የማዕድናት

4. የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንስኤ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ዛፍ መትከል　　ለ. የእንስሳት ፅዳጅን መጠቀም

   ሐ. ሕገ-ወጥ አደን　　መ. እርከን መሥራት

5. የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ውጤት የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የአየር ብክለት　　　　　　ለ. የበሽታ መስፋፋት

ሐ. የውሃ እጥረት　　　　　　መ. ሁሉም

## 3.4. በትምህርት ቤትና በቀበሌያችሁ የሚስተዋሉ ተገቢና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- ብክለትን ለመቀነስ የሚያግዙ የመፍትሔ ሀሳቦችን ታቀርባላችሁ፡፡
- በትምህርት ቤታችሁና በቀበሌያችሁ መልሶና ደጋግሞ የመጠቀም ዘዴዎችን ታዘወትራላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ብክለት
- የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች
- መልሶና ደጋግሞ መጠቀም

ቆሻሻ ማለት ምርቶች የመጀመሪያ አገልግሎታቸውን ከጨረሱ በኋላ የሚገኝ ተረፈ ምርት ነው፡፡ ነገር ግን ቆሻሻዎች በራሳቸው ሀብቶች ናቸው፡፡

ተማሪዎች! የምታውቋቸውን ተገቢ የሆኑና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎችን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡





ሥዕል 13 ተገቢ ያልሆነ የቆሻሻ አወጋገድ



ሥዕል 14 ተገቢ የሆነ የቆሻሻ አወጋገድ

የቡድን ውይይት 8

ዓላማ፦ ተገቢና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎችን መለየት

መመሪያ፦ ተማሪዎች! አምስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ በአካባቢያችሁ የተመለከታችኋቸውን የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች ተገቢና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች በማለት ከፍላችሁ በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

ብክለት በአንድ አከባቢ በሚገኙ ሀብቶች ላይ ጎጂ የሆነ ነገር መጨመር ነው፡፡

ብክለትን ለመቀነስ የሚያግዙ ተገቢ የሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች፡-

ቆሻሻን አለማቃጠል፡- ቆሻሻን ማቃጠል አየርን ስለሚበክል ማቃጠል የለብንም፡፡

ቆሻሻን በየቦታው አለመጣል፡- አካባቢን ስለሚያቆሽሽ ቆሻሻን በየቦታው መጣል የለብንም፡

የቆሻሻ ማጣራቀሚያ ገንዳ ማዘጋጀት፡- የተጠራቀሙት ቆሻሻዎች መልሰው አገልግሎት ላይ ስለሚውሉ ማጠራቀሚያ እቃዎች ውስጥ ማስቀመጥ ተገቢ ነው፡፡

ለማሕበረሰቡ የግንዛቤ ትምህርት መስጠት፡- ለማህበረሰቡ ስለቆሻሻ ምንነትና አወጋገድ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በመስጠት ቆሻሻዎችን በአግባቡ እንዲሰበስቡና እንዲጠቀሙ ማድረግ ይቻላል፡፡

ፋብሪካዎች ማጣሪያ እንዲጠቀሙ ማድረግ፡- ፋብሪካዎች የሚለቋቸውን ጭሶች፣ ደረቅና ፈሳሽ ተረፈ ምረቶች አካባቢን ከመበከላቸው በፊት በአግባቡ አጣርቶ ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡

የተጠቀምንበትን ዕቃ መልሶና ደጋግሞ መጠቀም፡- የተጠቀምንባቸውን ምርቶች ከመጣል ይልቅ መልሶና ደጋግሞ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የመጠጥ ጠርሙሶችን፣ የፕላስቲክ እቃዎችን (ፌስታልና ሀይላንድ) ደጋግሞ መጠቀም እንዲሁም የወዳደቁ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን (ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ኮምፒዩተር፣ ስልክ...)፣ የፕላስቲክ እቃዎችን፣ ወረቀቶችን፣ የወዳደቁ ብረቶችን፣ የምግብ ተረፈ ምርቶችንና ሌሎችን መልሶ መጠቀም የአካባቢ ብክለትን ለመቀነስ ይጠቅማል፡፡

ተግባር 4

ዓላማ፡- ተገቢ የሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎችን በተግባር ማሳየት

መመሪያ፡-ተማሪዎች! በትምህርት ቤታችሁና በቀበሌያችሁ የሚስተዋሉ ተገቢ የሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎችን በመጠቀም በትምህርት ቤታችሁ ግቢ ውስጥ ያሉትን ቆሻሻዎች አስወግዳችሁ ስለተጠቀማችሁበት አወጋገድ ዘዴዎች በክፍል ውስጥ ማብራሪያ ስጡ፡፡

መልመጃ 3.4

ሀ. ከታች በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ተገቢ የሆኑና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎችን ጻፉ፡፡

| ተ.ቁ | ተገቢ የሆነ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች | ተገቢ ያልሆነ የቆሻሻ አወጋገድ |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

## 3.5. ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ተፅዕኖዎች

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡

- ቆሻሻን ያለ አግባብ ማስወገድ በአካባቢያችሁ ላይ የሚያመጣውን ተፅዕኖ ትገልጻላችሁ፡፡
- ንጽህናው የተጠበቀ አካባቢ የሚሰጠውን ጠቀሜታ በተመለከተ ሀሳብ ትሰጣላችሁ፡፡

ተማሪዎች! ተገቢ ያልሆነ የቆሻሻ አወጋገድ ምን አይነት ተፅዕኖ እንደሚያስከትል ተናገሩ፡፡



ሥዕል 15 የውሃ መፍሰሻ ቦይ በቆሻሻ ተዘግቶ ጎርፍ ሲከሰት



ሥዕል 16 ያለአግባብ ቆሻሻ የተጣለበት አካባቢ

**ንጽህናው የተጠበቀ አካባቢ የሚሰጠው ጠቀሜታ፡-** ሥራን ደስተኛ ሆኖ ለመሥራት፣ ለመዝናናት፣ በሽታን ለመከላከል፣ ንፁህ አየር ለማግኘት፣ ጎብኝዎችን ለመሳብ፣ ደስተኛ ሆኖ ለመኖርና ለመሳሰሉት ይጠቅማል፡፡

የቡድን ውይይት 9

ዓላማ፡- ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ተጽዕኖዎችን መግለፅ

መመሪያ፡- ተማሪዎች! አምስት የሚደርሱ አባላት ያለው ቡድን በመመስረት ከዚህ በታች በቀረበው ጥያቄ ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

1. ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ተጽዕኖዎችን ዘርዝሩ።

ተማሪዎች! ከውይይታችሁ እንደተረዳችሁት ተገቢ ያልሆነ የቆሻሻ አወጋገድ የተለያዩ ተፅዕኖዎችን ያስከትላል። እነዚህም፡-

ጎርፍ፡- የውሃ መፍሰሻ ቦይ ውስጥ ቆሻሻዎችን መጣል ዝናብ በሚዘንብበት ሰዓት ውሃው መፍሰሻ ሲያጣ ጎርፍ ይከሰታል።

የአካባቢ ብክለት፡- ቆሻሻዎች በየአካባቢው ያለአግባብ ሲጣሉ ውሃ፣ አየር፣ አፈር፣ ምግብና የመሳሰሉት እንዲበከሉ ያደርጋል።

የበሽታ መስፋፋት፡- ቆሻሻ በአግባቡ ካልተወገደ ውሃ፣ አየር፣ ምግብና የመሳሰሉት ስለሚበከሉ በሽታዎች በቀላሉ እንዲፈጠሩና እንዲስፋፉ ያደርጋል። ለምሳሌ፡- ጉንፋን፣ የአንጀት ተስቦ፣ ተቅማጥ፣ ወስፋትና የመሳሰሉት በሽታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል።

## መልመጃ 3.5

ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።

1. ብክለትን ለመቀነስ የሚጠቅመው ዘዴ የቱ ነው?

   ሀ. ቆሻሻን በየቦታው መጣል　　ለ. በየቦታው መፀዳዳት

   ሐ. ቆሻሻን አለማቃጠል　　መ. ቆሻሻን በቤት ውስጥ ማቆየት

2. ሊበከል የሚችለው የቱ ነው?

ሀ. ውሃ ለ. ምግብ ሐ. አየር መ. ሁሉም

3. ቆሻሻን በአግባቡ አለማስወገድ የሚያስከትለው ተፅዕኖ የቱ ነው?

ሀ. የጎርፍ መከሰት ለ. ፅዱ አከባቢን መፍጠር

ሐ. ጤናማ ማሕበረሰብን መፍጠር መ. ተስማሚ አየር መኖር

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡**

1. ንፅህናው የተጠበቀ አካባቢ የሚሰጠውን ጥቅም ፃፉ፡፡

2. በአከባቢያችሁ የሚስተዋሉ የመልሶና ደጋግሞ የመጠቀም ዘዴዎችን ጥቀሱ፡፡

## ማጠቃለያ

- የአየር ሁኔታ በአንድ አካባቢ ከጊዜና ከቦታ አንፃር በየጊዜው የሚለዋወጥ የአየር ባህርይ ነው።
- አራት ዓይነት ወቅቶች አሉ። እነርሱም፦ ፀደይ፣ በጋ፣ በልግና ክረምት ናቸው።
- የአየር ንብረት በአንድ አካባቢ የሚታይ የአየር ሁኔታ ነው።
- የተፈጥሮ ሀብት በተፈጥሮ አካባቢ የሚገኝና ለሰው ልጅ ጥቅም የሚሰጥ ነገር ነው።
- ሰው ሰራሽ ሀብቶች የሰው ልጅ ዕውቀቱን፣ ጥበቡንና ሀብቱን በመጠቀም የሰራቸው ሀብቶች ናቸው።
- የተፈጥሮ ሀብቶች በርካታ ጥቅሞች አሏቸው። ለምሣሌ፦ ዕጽዋት ለምግብነት፣ ለግንባታ ሥራ፣ ለዱር እንስሳት መጠለያነት፣ ንፁህ አየር ለማግኘት ለመሳሰሉት ይጠቅማል።
- የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ሀብቶች በመጠን እና በዓይነት እየቀነሱ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው።
- አገር በቀልና የተለመዱ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ ዘዴዎች የሚባሉት እርከን መሥራት፣ አዝርዕትን አፈራርቆ መዝራት፣ አግድም ማረስ፣ የእንስሳት ፅዳጅን (ፍግ) መጠቀምና የመሳሰሉት ናቸው።
- ብክለትን ለመቀነስ የሚጠቅሙ የመፍትሔ ሐሳቦች ቆሻሻን አለማቃጠል፣ በየቦታው አለመጣልና በማጠራቀሚያ ዕቃ ውስጥ ማስቀመጥ፣ ፋብሪካዎች ማጣሪያ እንዲጠቀሙ ማድረግ፣ እፅዋት መትከልና የመሳሰሉት ናቸው።
- ተገቢ ባልሆነ የቆሻሻ አወጋገድ ምክንያት ከሚፈጠሩ ተፅዕኖዎች መካከል የበሽታ መስፋፋት፣ የጎርፍ መከሰት፣ የአካባቢ መበከልና የመሳሰሉት ናቸው።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች በማንበብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. የአየር ንብረት በየጊዜው የሚለዋወጥ የአየር ባህርይ ነው።
2. የተፈጥሮ ሐብቶች ጉዳት እንዳይደርስባቸው መንከባከብ አለብን።
3. ሁሉም ወቅቶች ተመሳሳይ የአየር ሁኔታ አላቸው።
4. ቆሻሻን በአግባቡ ማስወገድ የአከባቢ ብክለትን ለመቀነስ ይጠቅማል።
5. እርከን መሥራት ሀገር በቀል የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ዘዴ ነው።

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።**

1. የተፈጥሮ ሀብት የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. አደባባይ ለ. አፈር ሐ. ቤተ-መንግሥት መ. ሐውልት

2. ብክለትን ለመቀነስ የማይጠቅመው የቱ ነው?

   ሀ. ቆሻሻን በአግባቡ አለማስቀመጥ ለ. ቆሻሻን ማቃጠል

   ሐ. ቆሻሻን በየቦታው አለመጣል መ. በየቦታው አለመፀዳዳት

3. የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንስኤ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ሕገ-ወጥ አደን ለ. የሕዝብ ቁጥር መጨመር

   ሐ. የደን መጨፍጨፍ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

4. ሀገር በቀል የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ዘዴ ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. የእንስሳት ፅዳጅ መጠቀም ለ. እርከን መሥራት

   ሐ. ዛፍ መቁረጥ መ. አግድም ማረስ

5. ከሚከተሉት መካከል ለቱሪስት መስሕብነት የሚያገለግለው የቱ ነው?

ሀ. ጥንታዊ ቦታዎች ለ. የተፈጥሮ ዕፅዋት

ሐ. የዱር እንስሳት መ. ሁሉም መልስ ናቸው

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከስር ከተቀመጠው ሠንጠረዥ ውስጥ ካሉት ቃላት ወይም ሐረጋት በመምረጥ ተገቢውን መልስ ባዶ ቦታው ላይ ሙሉ።

| | | |
|---|---|---|
| ብክለት | የተፈጥሮ ሀብት | የተፈጥሮ ሀብት መመናመን |
| የአየር ሁኔታ | የአየር ንብረት | |

1. በአንድ አከባቢ ለረዥም ጊዜ የሚታይ የአየር ፀባይ--------------
2. በተፈጥሮ አከባቢ የሚገኝና ለሰው ልጅ ጥቅም የሚሰጥ ነገር-----------
3. በአንድ አከባቢ በሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ጎጂ ነገር መጨመር-------
4. ሀብቶች በመጠን እና በዓይነት እየቀነሱ መሆናቸውን የሚያሳይ---------
5. በአንድ አከባቢ ከጊዜና ከቦታ አንፃር በየጊዜው የሚለዋወጥ የአየር ባህርይ------

መ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ።

1. የተፈጥሮ ሀብቶችን ጥቅም ዘርዝሩ።
2. ወቅቶች በስንት ይከፈላሉ? ስማቸውስ?
3. የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንስኤዎችን ፃፉ።
4. የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ውጤቶችን ዘርዝሩ።
5. ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎችን ግለፁ።

## ፍተሻ

ልታከናውኗቸው የምትችሏቸውን ተግባራት ለመግለጽ ይህን (✓) ምልክት በሳጥኖቹ ውስጥ አመልክቱ፡

1. የአየር ሁኔታንና የአየር ንብረትን ልዩነት እገልጻለሁ።
2. በተለያዩ ወቅቶች የሚጠበቁ የአየር ሁኔታዎችን እገልጻለሁ።
3. በወረዳችን የሚኖረውን የሙቀት መጠን ልዩነት እገመግማለሁ።
4. በወረዳችን የሚኖረውን የዝናብ መጠን ሥርጭት አወዳድራለሁ።
5. በወረዳችን የአየር ንብረትን የሚቆጣጠሩ ነገሮችን (ከፍታ፣ የደን ሽፋንና ከባሕር ያለው ርቀት) እለያለሁ።
6. የተፈጥሮና የሰው ሠራሽ ሀብቶችን ምንነት እገልጻለሁ።
7. በወረዳችን የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን እለያለሁ።
8. የተፈጥሮ ሀብቶችን እገልጻለሁ።
9. የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ምንነትን እገልጻለሁ።
10. በወረዳችን የሚስተዋሉ ዋና ዋና የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንሥኤዎችንና ውጤቶችን እገልጻለሁ።
11. በወረዳችን የሚዘወተሩ ሀገር በቀልና የተለመዱ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የእንክብካቤ ዘዴዎችን እገልጻለሁ፡
12. የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ለቀጣይ ትውልድ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ዋጋ እሰጣለሁ።
13. ብክለትን ለመቀነስ የሚያግዙ የመፍትሔ ሐሳቦችን አቀርባለሁ።
14. በትምህርት ቤቴና በቀበሌዬ መልሶና ደጋግሞ የመጠቀም ዘዴዎችን አዘወትራለሁ
15. ቆሻሻን ያለአግባብ ማስወገድ በአካባቢያችን ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖ እገልጻለሁ
16. ንጽሕናው የተጠበቀ አካባቢ የሚሰጠውን ጠቀሜታ በተመለከተ ሐሳብ እሰጣለሁ

# ምዕራፍ አራት

# ማኅበራዊ አካባቢ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-

- የባህልን ምንነት ትገልጻላችሁ::
- በወረዳችሁ የሚገኙ ባህላዊ ልማዶችን ታብራራላችሁ::
- በወረዳችሁ የሚገኘውን የተፈጥሮ ሀብት ለመጠበቅና ለመንከባከብ የሚያግዙ ባህላዊ ልምዶችን ትለያላችሁ::
- ባህላዊ ብዝኀነትን በሥነ-ጥበብ ታደንቃላችሁ::
- የአየር ንብረት በወረዳችሁ በሚንጸባረቁ ባህሎች ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ትገልጻላችሁ::
- በወረዳችሁ የሚከናወኑ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎችን ታብራራላችሁ::
- ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በወረዳችሁ በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖ ትለያላችሁ::
- የገበያ ምንነትን ትገልጻላችሁ::
- የተፈጥሮ ሀብትና ምርቶቻቸው (ውጤቶቻቸው) በገበያ ላይ የሚኖራቸውን ተቀባይነት ትገልጻላችሁ::
- በወረዳችሁ የሚገኙ የመጓጓዣ ዘዴዎችን ታብራራላችሁ::

የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች

4.2 የባህል ብዝኀነት

4.2. በወረዳችሁ የሚገኙ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች

## መግቢያ

ተማሪዎች! በሁለተኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ትምህርታችሁ ስለቤተሰብና ስለቀበሌያችሁ ማኅበረሰብ ተምራችኋል:: በዚህ ክፍል ደግሞ ስለወረዳችሁ የባህል ብዝኀነት ትማራላችሁ:: ከዚህ በተጨማሪ በወረዳችሁ ስላለው የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ትማራላችሁ::

ምዕራፉ ሲጠናቀቅ የሚጠበቅባችሁን ዕውቀትና ክህሎት እንድትቀስሙ ትምህርቱን በንቃት መከታተል አለባችሁ::

## 4.1 የባህል ብዝኀነት

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- የባህልን ምንነት ትገልጻላችሁ::
- በወረዳችሁ የሚገኙ ባህላዊ ልማዶችን ታብራራላችሁ::
- በወረዳችሁ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብትን ለመጠበቅና ለመንከባከብ የሚያግዙ ባህላዊ ልምዶችን ትለያላችሁ::
- ባህላዊ ብዝኀነትን በሥነ-ጥበብ ታደንቃላችሁ::
- የአየር ንብረት በወረዳችሁ በሚንጸባረቁ ባህሎች ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ትገልጻላችሁ::

ቁልፍ ቃላት

- ✓ ባህል
- ✓ የባህል ብዝኀነት
- ✓ የባህል ክዋኔ

## ሀ. የባህልና ባህላዊ ክዋኔዎች ምንነትና ምሳሌዎች

ተማሪዎች! ወደ ትምህርት ቤት ስትሄዱ ወይም ስትመለሱ እንዲሁም በምትኖሩበት ወረዳ ብዙ ሰዎችን ታያላችሁ። የሚያጋጥሟችሁ ሰዎች ሁሉ አንድ አይነት ቋንቋ ይናገራሉ? ተመሳሳይ አለባበስ አላቸው?

በወረዳችሁ የሚኖረው ማኀበረሰብ የተለያየ ቋንቋ፣ ኃይማኖት፣ አመጋገብ፣ ሙዚቃ፣ አለባበስና የመሳሰሉት አሉት። ይህ የሚያሳየው በአካባቢያችሁ የተለያዩ ባህሎች መኖራቸውን ነው።

የቡድን ውይይት 1

ዓላማ፦ የባህል ምንነትን መለየት

መመሪያ፦ አምስት አባላት ያለው ቡድን በመመስረት በመወያያ ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን በደብተራችሁ ላይ ፅፋችሁ በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

የመወያያ ጥያቄዎች፦

1. ባህል ምንድን ነው?
2. የባህል ብዝኀነት ምንድን ነው?
3. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን የባህል መገለጫዎች ዘርዝሩ።



ሥዕል 1.የተለያዩ የአለባበስ ባህሎች

ባህል ማለት የአንድ ማኅበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ ነው። አንድ ማኅበረሰብ ማንነቱ የሚታወቀው በባህሉ ነው። እያንዳንዱ ማኅበረሰብ የራሱ ባህል አለው።

ለምሣሌ፦ ቋንቋ፣ ኃይማኖት፣ ምግብና አመጋገብ ፣ ልብስና አለባበስ ፣ ዘፈንና ጭፈራ ፣ ሠርግ ፣ ሰላምታ አሰጣጥና የመሳሰሉት የአንድ ማኅበረሰብ የባህል መገለጫዎች ናቸው።

ባህል ያድጋል፤ ከትውልድ ወደ ትውልድም ይሸጋገራል።

የባህል ብዝኀነት የተለያየ ባህል ያላቸው ሰዎች የባህል ልዩነታቸውን እንደያዙና አንዱ ሌላውን እንዳከበረ የሚኖርበት የማኅበራዊ ሕይወት ሥርዓት ነው። በቁጥር ትንሽ የሆነው ማኅበረሰብም ሆነ በቁጥር ብዙ የሆነው ማኅበረሰብ የሁለቱም ባህሎች እኩል ይከበራሉ።

እንዲሁም የባህሎች የዕድገት ደረጃ ቢለያይም ሁሉም ባህሎች ክቡር ናቸው።

ስለሆነም የባህል ብዝኀነት ሲባል መከባበርን ፣ ልዩነት ማድነቅን ፣ መቻቻልን ፣ አንዱ ከሌላው በጎ በጎውን መማርን ያጠቃልላል።

ተግባር 1

ዓላማ፦ የባህል ብዝኃነትን በሥነ-ጥበብ ማድነቅ

*መመሪያ፦ ተማሪዎች! አምስት አባላት ያለውን ቡድን በመመስረት በተለያዩ የሀገር ውስጥ ቋንቋዎች የተዘፈኑ ዘፈኖችን አጥንታችሁ አቅርቡ። ካቀረባችሁ በኋላም ከባህል ብዝኃነት ጋር ስላላቸው ትስስር የተረዳችሁትን ፍሬ ሐሳብ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ።*

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ሙዚቃ አንዱ የባህል መገለጫ ነው። የሚዘፈንበት ቋንቋም እንዲሁ ሌላው የባህል መገለጫ ነው። በቡድን ሥራው ወቅት እንደተመለከታችሁት የቀረቡት ዘፈኖች ቋንቋዎቻቸው ይለያያሉ። ቢሆንም አንዱን ከሌላው ሳናበላልጥ ሁሉንም በእኩል ማክበር አለብን። ምክንያቱም የእኛ ባህል ሊከበር የሚችለው የሌሎችን ባህል ስናከብር ነው። ይህ ሲሆን የሁሉም ባህል ይከበራል።

**የባህል ክዋኔ** አንድ የባህል መገለጫ ነው። በአንድ ማኅበረሰብ የቀን ተቀን ሕይወት ውስጥ የሚታዩ ድርጊቶች ናቸው። የባህል ክዋኔዎች ከማኅበረሰብ ማኅበረሰብ ሊለያዩ ይችላሉ።

ለምሣሌ፦ ኃይማኖታዊ ክዋኔዎች፣ ባህላዊ የሕክምና መንገዶች፣ ባህላዊ የመኖርያ ቤት አሠራር፣ ባህላዊ አስተዳደር ፣ ባህላዊ የግጭት አፈታት፣ ባህላዊ ደስታና ሐዘንን የመግለፅ መንገዶችና የመሳሰሉት ናቸው።






ሥዕል 2. የተለያዩ ኃይማኖታዊና ባህላዊ ክዋኔዎች




ሥዕል 3. የተለያየ አይነት ልጆችን የመንከባከብ ክዋኔ

## ለ. በወረዳችሁ የሚገኙ የተለያዩ ባህሎች

ተግባር 2

ዓላማ፡- በወረዳችሁ የሚገኙ ባህላዊ ልማዶች ምን ምን እንደሆኑ መግለፅ

መመሪያ፡- ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ ታላላቅ ሰዎችን (አዛውንቶችን) በመጠየቅ በወረዳችሁ ያሉ የተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎችን በመሰብሰብ በክፍል ውስጥ በማቅረብ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩበት።

ባህል ከአካባቢ አካባቢ ይለያያል። ሁሉም አካባቢ ያለው ባህል አንድ ዓይነት አይደለም። በቋንቋ ፣ በኃይማኖት ፣ በአመጋገብ ፣ በግጭት አፈታትና በመሳሰሉት ላይ የባህል

ልዩነቶች አሉ። ምክንያቱ ደግሞ ሰዎች ባህሎቻቸውን ከወላጆቻቸው ፣ ከትምህርት ቤት ወይም ካደጉበት ማኅበረሰብ ስለሚማሩ ነው። ወላጆቻቸው ስለሚለያዩ ፣ የተማሩባቸው ትምህርት ቤቶች ተመሳሳይ ስላልሆኑ፣ ያደጉበት አካባቢም የተለያየ በመሆኑ ምክንያት ባህሎቻቸው ሊለያዩ ችለዋል።

ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች በተጨማሪ የአየር ንብረትም ባህሎች እንዲለያዩ ሊያደርግ ይችላል። እስቲ የሚከተለውን ፎቶ በመመልከት የአካባቢውን የአየር ንብረት ምን እንደሆነ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ። በተለምዶ ወፍራም ልብስ የሚለበሰው በሙቀት ጊዜ ነው? ወይስ በብርድ ጊዜ?



ሥዕል 4. ብርድን የሚከላከል ልብስ

የአየር ንብረት በተለያዩ ወረዳ በሚታዩ አለባበሶች ላይ ተፅዕኖ አለው። ሞቃታማ የአየር ንብረት ባላቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ማኅበረሰብ ስስ ልብሶችን ያዘወትራሉ። የአየር ንብረቱ ቀዝቃዛ በሆነባቸው ስፍራዎች ወፈር ያሉ ልብሶችን መልበስ የተለመደ ነው። ስለዚህ የአየር ንብረት የአለባበስ ባህል ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል።

ተግባር 3

የግል ሥራ

ዓላማ፦ የአየር ንብረት በወረዳችሁ ባሉ ባህሎች ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ መግለጽ።

መመሪያ፦ ተማሪዎች! ታላላቆቻችሁን በመጠየቅና ከላይ የተጠቀሰውን የአለባበስ ባህልን ምሣሌ መሰረት በማድረግ የአየር ንብረት በሌሎች የወረዳችሁ ባህሎች ላይ የሚያመጣውን ተፅዕኖ ዘርዝሩ።

## ሐ. በወረዳችሁ ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ የሚረዱ ባህላዊ ክዋኔዎች

ተግባር 4

እንግዳ መጋበዝ

ዓላማ፦ በወረዳችሁ ለተፈጥሮ ሀብት (አፈር፣ ውሃ፣ እንስሳትና የመሳሰሉት) ጥበቃና እንክብካቤ የሚረዱ ባህላዊ ክዋኔዎችን ማብራራት።

መመሪያ፦ ተማሪዎች! መምህራችሁ የጋበዙላችሁን አዛውንት በክብር በመቀበል፣ ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ የሚረዱ ባህላዊ ክዋኔዎችን በተመለከተ የሚያደርጉላችሁን ገለፃ በጥሞና በማዳመጥ ያልተረዳችኋቸውን ነጥቦች እንግዳውን በትሕትና ከጠየቃችሁ በኋላ ከገለፃው ያገኛችኋቸውን ቁምነገሮች ለመምህራችሁ ተናገሩ።



ሥዕል 5. ተገቢውን እንክብካቤ የተደረገለት ደን

በምዕራፍ ሦስት የተማራችኋቸው ሀገር በቀል የተፈጥሮ ሀብት የመጠበቅ ዘዴዎች አሉ፡፡ ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ የሚረዱ ባህላዊ ክዋኔዎችም ከዚሁ ጋር በእጅጉ ተዛማጅ ነው፡፡ በአከባቢያችን ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ የሚረዱ ባህላዊ ክዋኔዎች ከምንላቸው ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የእንስሳት ፅዳጅን ለእርሻ ሥራ መጠቀም፡- የእንስሳት ፅዳጅ (ፍግ) በመጠቀም የአፈርን ለምነት መጠበቅ ይቻላል፡፡ ይህም የግብርና ምርት እንዲጨምር ያደርጋል፡፡



ሥዕል 6. ከእንስሳት ፅዳጅ (ፍግ) የተገኘ ማዳበሪያ

2. እርከን መሥራት፦ ደግሞ ሌላው የተፈጥሮ ሀብትን የምንከባከብበት ባህላዊ ዘዴ ነው፡፡ እርከን ሲሰራ አፈርን፣ ውሃንና ዕጽዋትን ለመጠበቅ ይጠቅማል፡፡



ሥዕል 7. የእርከን ሥራ

3. አግድም ማረስ፡- ይህ አይነት ባህላዊ ዘዴም እንደዚሁ የአፈር መሸርሸርን ይከላከላል፡፡



ሥዕል 8. አግድም ማረስ

ከእነዚህ በተጨማሪ ማኅበረሰቡ በተለይም በኃይማኖት ሥፍራዎች ወፎችን መግደል ፣ ዛፎችን መቁረጥ እንዲሁም ተፈጥሮን በአጠቃላይ መጉዳት እንደነውር ይታያል። እንዲሁም ማኅበረሰቡ ሀብትን ሳያባክን በአግባቡ መጠቀም እንዳለበት በኃይማኖት አባቶች በየጊዜው ትምህርት ስለሚሰጠው የተፈጥሮ ሀብቶች የሚጠበቁበት ሌላው ባህላዊ መንገድ ነው።

ከላይ የተጠቀሱትና የመሳሰሉት የተፈጥሮ ሀብቶችን የምንጠብቅባቸው ባህላዊ መንገዶች ናቸው።

## መልመጃ 4.1

ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች በማንበብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ፣ ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. እርከን መሥራት የተፈጥሮ ሀብትን ለመጠበቅ አይጠቅምም።

2. መከባበር የባህል ብዝኀነት አንዱ መገለጫ ነው።

3. ኃይማኖታዊ ክዋኔ ከባህል ክዋኔዎች ውስጥ አንዱ ነው።

ለ. ሰንጠረዡ ውስጥ ስለባህል የተጠቀሰውን ዐረፍተ ነገር በማንበብ ትክክል ከሆነ (✓) ትክክል ካልሆነ (X) ምልክት በመጠቀም ሙሉ።

| | | |
|---|---|---|
| 1 | ባህል የአንድ ማኅበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ ነው። | |
| 2 | ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ ይሸጋገራል። | |
| 3 | የሁሉም ማኅበረሰብ ባህል ተመሳሳይ ነው። | |
| 4 | የሁሉም ባህሎች የዕድገት ደረጃ አንድ ዓይነት ነው። | |
| 5 | ባህሎች ሁሉ እኩል ናቸው። | |
| 6 | አየር ንብረት በባህል ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል። | |
| 7 | ባህል አያድግም። | |
| 8 | አንድ ማኅበረሰብ ማንነቱ የሚታወቀው በባህሉ ነው። | |

ሐ. የሚከተሉትን ሦስት ዐረፍተ ነገሮችን በአካባቢያችሁ በሚነገር ሌላ ቋንቋ በማስተርጎም ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

1. ባህሌን አከብራለሁ።

2. ይቅርታ አድርግልኝ!

3. በጣም አመሠግናለሁ።

## 4.2 በወረዳችሁ የሚገኙ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች

### ከርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፦

- በወረዳችሁ የሚከናወኑ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎችን ታብራራላችሁ::
- ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በወረዳችሁ የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖ ትለያላችሁ::
- የገበያ ምንነትን ትገልጻላችሁ::
- የተፈጥሮ ሀብትና ምርቶቻቸው በገበያ ላይ የሚኖራቸውን ልምድ ትገልጻላችሁ::
- በወረዳችሁ የሚገኙ የመጓጓዣ ዘዴዎችን ታብራራላችሁ::

**ቁልፍ ቃላት**

- ✓ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ
- ✓ ገበያ
- ✓ መጓጓዣ

**የቡድን ውይይት 2 ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎችን መዘርዘር**

መመሪያ፦ ተማሪዎች! ከ 5-7 አባላት የያዘ ቡድን መስርታችሁ በሚከተሉት የመወያያ ጥያቄዎች ላይ ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን በተወካዮቻችሁ አማካኝነት በክፍል ውስጥ አቅርቡ::

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ምንድን ነው?
2. በአካባቢያችሁ የምታስተውሏቸውን ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ዘርዝሩ።

ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ማለት ማንኛውም ገቢ የሚያስገኝ ሕጋዊ የሥራ መስክ ነው። ሰዎች ኑሯቸውን ለመምራት የሚያከናውኗቸው የሥራ ዘርፎች ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ይባላሉ። ሥራ ደግሞ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላትና ራስን ለመቻል የሚከናወን፣ በሰው የሚፈጠር ተግባር ነው። የማይሰሩ ሰዎች ለኑሮ የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች ማሟላት ስለማይችሉ ዘወትር ይቸገራሉ።

ዋና ዋና የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች የሚባሉት ንግድ፣ ኢንዱስትሪ፣ እደ-ጥበብና ግብርና ናቸው።

**ተግባር 5**

**የግል ሥራ**

**ዓላማ፡** በወረዳችሁ የሚገኙ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎችን ማብራራት

**መመሪያ፡** ተማሪዎች! ከላይ የተዘረዘሩት ዋና ዋና የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎችን መነሻ በማድረግ ቤተሰቦቻችሁ በእያንዳንዱ የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጧችሁ በመጠየቅ ያገኛችሁትን መልስ በጽሑፍ ከመዘገባችሁ በኋላ ሀሳባችሁን በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

1. ንግድ



ሥዕል 9. የንግድ እንቅስቃሴ

ተግባር 6

ድራማ

ዓላማ፦ የንግድ ምንነትና ጠቀሜታ መለየት

መመሪያ፦ ተማሪዎች! በመጀመሪያ ሰባት ሰባት አባላት ያላቸው ሁለት ቡድኖችን መስርቱ:: በመቀጠልም አንዱ ቡድን 'ሻጮች'፣ ሌላኛውን ቡድን 'ገዢዎች' በማለት ተመዳደቡ:: ከዚያም በየቤታችሁ ከሄዳችሁ በኋላ ሻጮቹ ቡድን ዋጋቸው እስከ አሥር ብር የሚያወጡ የተለያዩ በአካባቢያችሁ የሚሸጡ ዕቃዎችን በወረቀት ላይ በመሳል አዘጋጁ:: የገዢዎቹ ቡድን ደግሞ መቶ ብርና ከዚያ በታች ያሉ ብሮችን በወረቀት መልክ አዘጋጅታችሁ ቅረቡ:: በመጨረሻም በክፍል ውስጥ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግብይትን በድራማ መልክ አቅርቡ:: የድራማው ተመልካቾች የሆናችሁ ልጆች ደግሞ ድራማውን በጥሞና ተከታተሉና ከተመለከታችሁት ድራማ በመነሳት ንግድ ምን እንደሆነ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ::

ንግድ በሰዎች መካከል የሚከናወን ዕቃን ወይም አገልግሎትን የመሸጥ ፣ የመግዛትና የመለዋወጥ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ነው። ገንዘብ ደግሞ በንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ ጉልህ ሚና አለው።

ንግድ አምራቾችንና ተጠቃሚዎችን ያገናኛል። ሻጮች ገንዘብ እንዲያገኙ፣ ገዢዎች ደግሞ ፍላጎታቸው እንዲሟላ ያደርጋል። በዚህም ምክንያት ሻጮችም ሆኑ ገዢዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ። ንግድ ማኅበራዊ ግንኙነት ከማጠናከር አንፃርም ጠቃሚ ነው።

ንግድ በሁሉም ወረዳዎች ጎልቶ የሚታይ የሥራ ዘርፍ ነው። በተለያዩ ወረዳዎች የጅምላ ንግድና የችርቻሮ ንግድ ይካሄዳል።

## 2. ኢንዱስትሪ



ሥዕል 10. ኢንዱስትሪ

**የቡድን ውይይት 3**

ዓላማ፡ የኢንዱስትሪ ምንነትና ጠቀሜታ መለየት

*መመሪያ፡* ተማሪዎች! ከ4 እስከ 6 ተማሪዎች በቡድን በመሆን ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

1. ኢንዱስትሪ ማለት ምንድን ነው?
2. በወረዳችሁ የሚገኙ ኢንዱስትሪዎች የሚያመርቷቸውን ምርቶች ዘርዝሩ።

ኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃዎችን ዘመናዊ መሣሪያዎች በመጠቀም በአጭር ጊዜና በቀላል መንገድ ለገበያነት የሚቀርቡ ዕቃዎችን የማምረት ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ነው።

በወረዳዎቻችሁ ውስጥ የጨርቃ ጨርቅ፣ የጫማ፣ የዕንጨት ውጤቶች፣ የቆዳ ውጤቶች፣ የብረታ ብረት፣ የሕንፃ መሣሪዎያች፣ የሕትመት ውጤቶች፣ የኬሚካል ውጤቶች፣ የመጠጥና የታሸጉ ምግቦች ፋብሪካዎች ይገኛሉ።

### 3. እደ-ጥበብ






ሥዕል11. የተለያዩ የእደ-ጥበብ ውጤቶች

ተማሪዎች! ስዕሎቹ ምን ያሳያሉ?

እደ-ጥበብ ሰዎች እጃቸውን ወይም ትንንሽ መሣሪያዎችን በመጠቀም ዕቃዎችን የሚያመርቱበት የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የባህል ልብሶች፣ የሸክላ ሥራዎች፣ የቀርከሃ ሥራዎች፣ የብረታ ብረት፣ ጌጣጌጥ፣ የቆዳ ሥራዎችና የመሳሰሉትን ዕቃዎች በእጅ የሚሰሩ የእደ ጥበብ ውጤቶች ናቸው፡፡

በሲዳማ ክልል በተለያዩ የወረዳ አካባቢዎች በርካታ ሀገር በቀል የእደ- ጥበብ ውጤቶች ይመረታሉ፡፡

## ተግባር 7

ጉብኝት

ዓላማ፡- የእደ-ጥበብ ውጤቶች ጠቀሜታን መለየት

መመሪያ፡- ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ የሚገኙ የእደ-ጥበብ ሥራ የሚያከናውኑ ግለሰቦችን ወይም ድርጅቶችን ከታላላቆቻችሁ ጋር በመሆን ከጎበኛችሁ በኋላ በሚከተሉት ሐሳቦች ላይ ከባለሙያዎቹ ጋር በመወያየት በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

1. እደ-ጥበብ ለማኅበረሰብ የሚሰጠው ጥቅም ምንድን ነው?
2. የእደ-ጥበብ ውጤቶችን ለማምረት የምንጠቀማቸው ጥሬ ዕቃዎች ምን ምን ናቸው?
3. ባህልን ከመጠበቅ አንፃር እደ-ጥበብ ምን ጥቅም አለው?

## 4. ግብርና



ሥዕል 12. የተለያዩ የግብርና ዓይነቶች

የቡድን ውይይት 4

ዓላማ፦ የግብርና ምንነትና ጠቀሜታ መለየት

መመሪያ፦ ተማሪዎች! አራት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

1. ግብርና ምንድን ነው?
2. በግብርና የሚመረቱ ምርቶች ምን ምን ናቸው?

ግብርና በጣም አስፈላጊ የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ነው። ምክንያቱም የሰው ልጅ በሕይወት ለመኖር መሰረታዊ የሆነውን ምግብ የሚያመረተው በግብርና ሥራ ነው።

ግብርና በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል። እነርሱም፦ እርሻና የእንስሳት እርባታ ናቸው። በእርሻ ሥራ የሚተዳደሩ ሰዎች አርሶ አደሮች ይባላሉ። በእንስሳት እርባታ የሚተዳደሩት ደግሞ አርብቶ አደሮች ይባላሉ። ግብርና የምግብ ምንጭ ነው። ለኢንዱስትሪና ለእደ-ጥበብ ጥሬ ዕቃዎችን ያቀርባል።

በሲዳማ ክልል በተለያዩ ወረዳዎች በሚገኙ የገጠር የእርሻ መሬቶች እና የመኖሪያ ግቢዎች ውስጥ ልዩ ልዩ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች ይመረታሉ። እንዲሁም የእንስሳት እርባታ አለ።

በአጠቃላይ በሁሉም ወረዳዎች ተመሳሳይ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ላይኖር ይችላል። ለምሳሌ፡- የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር እና የይርጋለም ከተማ አስተዳደር የሲዳማ ክልል የኢዱስትሪ ቀጠና በመሆን ብዛት ያላቸው ኢንዱስትሪዎችን ይይዛሉ።

## መልመጃ 4.2

ሀ. በ ‘ሀ’ ስር ለተዘረዘሩት ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በ ‘ለ’ ስር ከተዘረዘሩት ምሳሌዎች ጋር በትክክል አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ግብርና | ሀ. የችርቻሮ ሱቅ |
| 2. ኢንዱስትሪ | ለ. የሸክላ ሥራ |
| 3. እደ-ጥበብ | ሐ. ዶሮ እርባታ |
| 4. ንግድ | መ. ብረታብረት ፋብሪካ |

ለ. የሚከተሉትን ድርጊቶች በማንበብ ሥራ ከሆነ “አዎ” ሥራ ካልሆነ “አይደለም” በማለት መልሱ።

| ተ.ቁ | ድርጊቶች | አዎ/አይደለም |
|---|---|---|
| 1 | ስርቆት | |
| 2 | መምህርነት | |
| 3 | ልመና | |
| 4 | አስመጪና ላኪ | |
| 5 | ጋዜጠኝነት | |

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ቤተሰብን በማወያየት ዘርዘር ያለ ማብራሪያ ፃፉ።

1. ከምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እናንተ ስታድጉ መሆን የምትፈልጉት ምንድን ነው? ለምን? ዘርዘር ያለ ጽሑፍ በመፃፍ በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

## ሀ. በወረዳችሁ በተፈጥሮ ሀብት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚሳድሩ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች

የቡድን ውይይት 5

ዓላማ፦ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በወረዳችሁ በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚሳድሩትን አሉታዊ ተፅዕኖ መለየት

መመሪያ፦ ተማሪዎች! በመጀመሪያ አራት አባላት ያሉት ቡድን መስርቱ፡፡ በመቀጠልም መምህራችሁ የሰጧችሁን የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ርዕስ በወረዳችሁ የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ በመወያየት ያገኛችኋቸውን መልሶች በተወካያችሁ አማካኝነት በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

ሕይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ ለመኖር የተፈጥሮ ሀብቶች ያስፈልጓቸዋል፡፡ ለምሳሌ፡ - ሰዎች የተፈጥሮ አየርን ይተነፍሳሉ፤ ውሃን ይጠቀማሉ፤ እንዲሁም ከዕንጨትና ከሌሎች ማዕድናት መኖሪያቸውን ይገነባሉ፡፡ እነዚህ በርካታ ጥቅሞች የሚሰጠንን የተፈጥሮ ሀብት መንከባከብና መጠበቅ አለብን፡፡

ነገር ግን አንዳንድ የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በተፈጥሮ ሀብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራሉ፡፡

ለምሣሌ፦ በንግድ ሥራ ውስጥ የፕላስቲክ ምርቶች አገልግሎታቸው ሲያበቃ በተገቢው መንገድ ካልተወገዱ ከባቢ አየርን ይበክላሉ፡፡ በተጨማሪ ምግብን አዘጋጅተው የሚሸጡ

አንዳንድ ግለሰቦች የማገዶ እንጨትን ለማግኘት ሲሉ ደንን ይጨፈጭፋሉ።





ሥዕል 13. የንግድ ሥራ በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ያለው አሉታዊ ተፅዕኖ

በሌላ በኩል ከኢንዱስትሪዎች የሚለቀቀው ጭስ አየርን ይበክላል። የፋብሪካዎቹ ፍሳሽ ቆሻሻ ደግሞ እንደውሃና አፈር ባሉ የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ትልቅ ጉዳት ያደርሳል።





ሥዕል 14. የኢንዱስትሪ ሥራ በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ያለው አሉታዊ ተፅዕኖ

የዕንጨት ሥራ፣ የሸክላ ሥራና የመሳሰሉ የእደ-ጥበብ ሥራዎች ደን እንዲጨፈጨፍና አፈር እንዲሸረሸር ምክንያት ይሆናሉ። ሰዎች ለግብርና ሥራ የሚሆን መሬት ለማግኘትም ደንን ይጨፈጭፋሉ።

በአጠቃላይ ብዙ የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች የሚጠቀሙት የተፈጥሮ ሀብቶችን

ነው:: በተጨማሪም ቆሻሻና ተረፈ ምርቶች በአግባቡ ባለመወገዳቸው ምክንያት ውሃን፣ ዕጽዋትንና አየርን ይበክላሉ:: ስለሆነም ሥራዎቹ ሲሰሩ የተፈጥሮ ሀብቶችን በማይጎዳ መልኩ እንዲሆን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል:: በሥራው ሂደት የሚገኙ ተረፈ ምርቶችንና ቆሻሻዎችን በተገቢው መንገድ ማስወገድ የተፈጥሮ ሀብትን ለመጠበቅ ይረዳል:: ምክንያቱም የተፈጥሮን ሀብቶች ከተበከሉ፣ ከተጎዱና ከጠፉ የሰው ልጅ በሕይወት መኖር አይችልም::

ተግባር 8

ድራማ

ዓላማ፦ የተፈጥሮ ሀብቶችን በመንከባከብና በመጉዳት መካከል ያለ ልዩነትን ማሳየት

መመሪያ፦ ተማሪዎች! 10 አባላት ያለው ቡድን በመመስረት “ደስተኛ አካባቢ” እና “የተከፋ አካባቢ” በሚል በሁለት ቡድን ተመዳደቡ:: “ደስተኛ አካባቢ” የሚባለው ቡድን ለተፈጥሮ ሀብቶቹ ተገቢውን እንክብካቤ አድርጎ ጥሩ ውጤት በማግኘት ደስተኛ የሆነውን አካባቢ ይወክላል:: “የተከፋ አካባቢ” የተሰኘው ቡድን ደግሞ የተፈጥሮ ሀብቶቹ የተጎዱበት አካባቢ በመወከል በድራማ መልክ አቅርቡ

## ለ.የገበያ ምንነት



ሥዕል 15. ገበያ

ተግባር 9

የግል ሥራ

ዓላማ፡- የገበያ ምንነትን መግለፅ

መመሪያ፡- የሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በመመስረት ቤተሰብን ጠይቃችሁ መረጃዎችን ከሰበሰባችሁ በኋላ በክፍል ውስጥ በማቅረብ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩበት።


1. ገበያ ምንድን ነው?
2. ቴክኖሎጂን በመጠቀም በቀጥታ መገበያየት ማለት ምን ማለት ነው?

ገበያ ማለት የንግድ ሥራ የሚከናወንበት ቦታ ነው። ገበያ ላይ የሚሳተፉት ሰዎች ገዥና ሻጭ ይባላሉ።

ልማዳዊ ግብይት ላይ ሻጮቹ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ይዘው ወደ ገበያ ሲቀርቡ ገዢዎቹ በበኩላቸው ገንዘብ ይዘው ይቀርባሉ። ይህ መገበያያ ቦታ ልዩ ህንፃ ኖሮት የሚከናወን ወይም ክፍት የሆነ ቦታ ላይ የሚከናወን ሊሆን ይችላል።

ዘመናዊ ግብይት ላይ ደግሞ ገዢው ወደ ገበያ በአካል መሄድ ሳይጠበቅበት የሚገዛውን ነገር በድህረ-ገፅ አማካኝነት ምስሉን አይቶ በመምረጥና ተገቢውን ክፍያ በመፈፀም ዕቃውን ይረከባል።





ሥዕል 16. ሀ. የተለምዶ ግብይት ለ. የዘመናዊ ግብይት

## ሐ. በወረዳችሁ ለገበያነት ሊቀርቡ የሚችሉ የተፈጥሮ ሀብቶችና ውጤቶች

የቡድን ውይይት 6


ዓላማ፦ በወረዳችሁ ለገበያነት ሊቀርቡ የሚችሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን መግለፅ

መመሪያ፦ ከ4 እስከ 6 ተማሪዎች በቡድን በመሆን ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

1. የተፈጥሮ ሀብት ምርቶችን (ውጤቶችን) ዘርዝሩ።
2. በአካባቢያችሁ ለገበያ ሊቀርቡ የሚችሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን ዘርዝሩ።

ተማሪዎች! በምዕራፍ ሦስት ትምህርታችሁ ስለተፈጥሮ ሀብት ምንነትና እንክብካቤ ተምራችኋል። የተፈጥሮ ሀብቶችን መንከባከብ ማኅበረሰብን ይጠቅማል። በተቃራኒው የተፈጥሮ ሀብቶችን መጉዳትና ዝቅተኛ ትኩረት መስጠት ደግሞ ለአደጋ ይዳርገናል።





ሥዕል 17. ለገበያነት ሊቀርቡ የሚችሉ የተፈጥሮ ሀብት ውጤቶች

ከተፈጥሮ ሀብቶች የተለያዩ ውጤቶችን ለገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ እንሆናለን። ለምሣሌ፦ የተፈጥሮ ውሃን በመንከባከብ የታሸገ ውሃ ለገበያ ማቅረብ ይቻላል። የተፈጥሮ ደኖችን በመንከባከብ የቤትና የቢሮ ዕቃዎችን መሥራት ይቻላል። አፈርን በመንከባከብ ደግሞ የተለያዩ የእደ-ጥበብ ውጤቶችን ለማምረት ያስችላል። ለዱር እንስሳት ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ጎብኚዎችን በመሳብ የገቢ ምንጭ ይሆናሉ።

## መ. በወረዳችሁ  የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት ውጤቶችና የግብይት ክዋኔዎች

የቡድን ውይይት  7

ዓላማ፦ በወረዳችሁ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት ውጤቶች የግብይት ክዋኔዎችን መግለፅ

መመሪያ፦  ከ5 እስከ 7 ተማሪዎች በቡድን በመሆን ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

1. በወረዳችሁ ገበያዎች ላይ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት ውጤቶችን ዘርዝሩ።
2. በወረዳችሁ በሚገኙ ገበያዎች ላይ የሚቀርቡ የተፈጥሮ ሀብት ውጤቶች የግብይት ክዋኔዎች ግለፁ።

በአካባቢያችሁ ገበያዎች የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብቶችና ውጤቶቻቸው ለሽያጭ ይቀርባሉ። ለምሳሌ፦ ተጣርቶ የታሸገ ውሃ ፣ የእንጨት ውጤቶች ፣ የሸክላ ሥራዎች፣ የማዕድን ውጤቶችና የመሳሰሉት በተለያየ መልክ ለገበያ ይቀርባሉ። እነዚህና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶችና ውጤቶቻቸው ለኑሮ ጠቃሚ በመሆናቸው ገበያ በሚቀርቡበት ጊዜ ከፍተኛ የሆነ ተፈላጊነት አላቸው። ጥሩ የገበያ ክዋኔ አላቸው። ነገር ግን የምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ ስላስገኙልን ብቻ እንክብካቤና ጥበቃን በመተው ልንጠቀምባቸው አይገባም። ምክንያቱም በእንክብካቤ እጥረት ይባክናሉ፤ እኛም እንጎዳለን። ከዚያም አልፎ በጣም ከተመናመኑ ህይወታችን አደጋ ውስጥ ይወድቃል።

## ሠ. ለሰዎችና ለዕቃዎች የሚያገለግሉ የተለያዩ የመጓጓዣ ዘዴዎች

የቡድን ውይይት 8

ዓላማ፦ በወረዳችሁ የሚገኙ የመጓጓዣ ዘዴዎችን ማብራራት

መመሪያ፦ ከ5 እስከ 7 ተማሪዎች በቡድን በመሆን ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

1. መጓጓዣ ምንድን ነው?
2. በወረዳችሁ የሚገኙ የመጓጓዣ ዘዴዎችን ጥቀሱ።

መጓጓዣ ሰዎችና ዕቃዎችን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚንቀሳቀሱበት ዘዴ ነው። መጓጓዣዎች ሰዎች ረዥም ርቀትን በአጭር ጊዜ ለመድረስ የፈጠሯቸው ዘዴዎች ናቸው።

የመጓጓዣ ዓይነቶች ሁለት ናቸው። እነርሱም፦ ባህላዊ መጓጓዣና ዘመናዊ መጓጓዣ ናቸው።

1. ባህላዊ መጓጓዣ፦ ሰዎችንና ምርቶችን በሰው፣ በአህያ፣ በበቅሎ፣ በፈረስና በግመል ከቦታ ቦታ የሚጓጓዙበት የመጓጓዣ ዓይነት ነው። ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነት ለብዙ ዘመናት አገልግሎት ላይ የዋለ ነው። አንዳንድ ከመሐል ከተማ ርቀው የሚገኙ ማኅበረሰቦች አሁንም ድረስ ባህላዊ መጓጓዣዎችን ይጠቀማሉ።



ሥዕል 18. ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነት ተጠቅሞ የሚጓዝ ሰው

2. ዘመናዊ መጓጓዣ፡- ሰዎችንና ምርቶችን በመኪና ፣ በባቡር ፣ በመርከብ ፣ በአውሮፕላን ከቦታ ቦታ የሚጓጓዙበት የመጓጓዣ ዓይነት ነው። ዘመናዊ የመጓጓዣ ዘዴዎች ውድና ፈጣን ናቸው።



ሥዕል 19. ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች

መጓጓዣዎች በአጠቃላይ ለህብረተሰቡ በርካታ ጥቅሞችን ይሰጣሉ። ለምሳሌ፡ ሰዎችን ወደ ሥራ ቦታ፣ ወደ ትምህርት ቤት፣ ወደ ሐኪም ቤትና የመሳሰሉት ማድረስና መመለስ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎችን ለማቀላጠፍ ፣ ዕቃዎች ለማጓጓዝና ምርት ለሸማቾች ለማድረስ ይጠቅማሉ።

## መልመጃ 4.3

**ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች በማንበብ ትክክል ከሆነ “እውነት” ትክክል ካልሆነ “ሐሰት” በማለት መልሱ።**

1. በድህረ-ገፅ አማካኝነት የሚካሄድ የግብይት ዓይነት ‘ኋላቀር ግብይት ነው።
2. ለተፈጥሮ ሀብቶች ዝቅተኛ ትኩረት መስጠት ለአደጋ ያጋልጣል።
3. መጓጓዣ ሰዎችና ዕቃዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚንቀሳቀሱበት ዘዴ ነው።
4. ፈረስ ከዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች ይመደባል።

**ለ. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተገቢው መልስ ሙሉ።**

1. ሰዎች፣ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በመግዛትና በመሸጥ የሚለዋወጡበት ቦታ ------------- ይባላል።
2. የመጓጓዣ ዓይነቶች --------------- እና --------------- ናቸው።

## ማጠቃለያ

- ባህል ማለት የአንድ ማኅበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ ነው። ባህሎች ሁሉ እኩል ናቸው።
- የባህል ብዝኀነት የተለያየ ባህል ያላቸው ሰዎች የባህል ልዩነታቸውን እንደያዙና አንዱ ሌላውን እንዳከበረ የሚኖርበት የማኅበራዊ ሕይወት ሥርዓት ነው።
- የባህል ክዋኔ አንድ የባህል መገለጫ ሲሆን በአንድ ማኅበረሰብ የቀን ተቀን ሕይወት ውስጥ የሚታዩ ድርጊቶች ናቸው።
- የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመጠበቅና ለመንከባከብ የሚረዱ ባህላዊ ክዋኔዎች አሉ።
- የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ የሚባለው ገቢ የሚያስገኝ ማንኛውም ሕጋዊ የሥራ መስክ ነው። ዋና ዋና የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች የሚባሉት ንግድ፣ ኢንዱስትሪ፣ እደ ጥበብና ግብርና ናቸው።
- ገበያ ማለት የንግድ ሥራ የሚከናወንበት ቦታ ሲሆን የሚሳተፉት ሰዎች ገዥና ሻጭ ይባላሉ።
- የተፈጥሮ ሀብት ውጤቶችን ለገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ እንሆናለን።
- መጓጓዣ ሰዎችና ዕቃዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚንቀሳቀሱበት ዘዴ ነው። የመጓጓዣ ዓይነቶች ሁለት ናቸው። እነርሱም፦ ባህላዊና ዘመናዊ ናቸው።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች በማንበብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. የአየር ንብረት በባህል ላይ ተጽዕኖ አለው።
2. ባህል ከአካባቢ አከባቢ ይለያያል።
3. ሥራ የማይሰሩ ሰዎች መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ማሟላት አይችሉም።
4. ንግድ ለሻጮች እንጂ ለገዢዎች ምንም ጥቅም የለውም።
5. በእንስሳት እርባታ የሚተዳደሩ ሰዎች አርብቶ አደሮች ይባላሉ።
6. የሁሉም የሲዳማ ክልል ወረዳዎች ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ተመሳሳይ ነው።
7. በዘመናዊው ግብይት ገዢዎች አንድን ዕቃ ወይም አገልግሎት ቤታቸው ሆነው በግዢ ማግኘት ይችላሉ።
8. በአሁኑ ሰዓት ባህላዊ የመጓጓዣ ዘዴዎች የሉም።
9. ዘመናዊ የመጓጓዣ ዘዴዎች ከባህላዊ ዘዴዎች የበለጠ ውድ ናቸው።
10. ሰዎች እጃቸውን ወይም ትንንሽ መሣሪያዎችን በመጠቀም ዕቃዎችን የሚያመርቱበት የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ እደ-ጥበብ ይባላል።

**ለ. ሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።**

1. ስለምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. የሥራ መስክ ነው ለ. ሕጋዊ ነው

   ሐ. ገቢ ያስገኛል መ. ሁሉም መልስ ናቸው

2. ሥራ ለምን ይጠቅማል?

ሀ. ራስን ለመቻል ለ. በሌሎች ላይ ጥገኛ ላለመሆን

ሐ. መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት መ. ሁሉም መልስ ናቸው

3. በእደ-ጥበብ የማይመረተው የቱ ነው?

ሀ. የባህል ልብስ ለ. የሸክላ ምጣድ

ሐ. የታሸገ ውሃ መ. የቀርከሃ ቅርጫት

4. የባህል ብዝሃነት ውስጥ አስፈላጊ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. መከባበር ለ. ልዩነት ማድነቅ

ሐ. መቻቻል መ. ሁሉም መልስ ናቸው

5. የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመጠበቅ የሚያግዝ ባህላዊ መንገድ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. የእንስሳት ፅዳጅን መጠቀም ለ. እርከን መሥራት

ሐ. ደን መጨፍጨፍ መ. የአግድም አስተራረስ

6. ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነት ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ባቡር ለ. ግመል ሐ. መርከብ መ. አውሮፕላን

ሐ. የሚከተሉት ያልተሟሉ ዐረፍተ ነገሮችን በማንበብ ክፍት ቦታውን በትክክል ሊያሟላ የሚችለው መልስ ከጥያቄው አስቀድሞ ከተዘረዘሩት ውስጥ በመምረጥ ሙሉ::

መጓጓዣ ንግድ ባህል

የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ኢንዱስትሪ

1. የአንድ ማኅበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ --------------ነው::
2. ማንኛውም ገቢ የሚያስገኝ ሕጋዊ የሥራ መስክ--------------ነው::
3. በሰዎች መካከል የሚከናወን ዕቃን ወይም አገልግሎትን የመሸጥና የመግዛት ሂደት ሂደት ------------- ይባላል::
4. ጥሬ ዕቃዎችን ዘመናዊ መሣሪያዎች በመጠቀም በአጭር ጊዜና በቀላል መንገድ ለገበያነት የሚቀርቡ ዕቃዎችን የማምረት ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ------------ ነው::
5. ሰዎችና ዕቃዎችን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚያንቀሳቅሱበት ዘዴ ------------- ነው::

መ. ከታች በቀረበው ሠንጠረዥ ውስጥ የሚገኙ ድርጊቶችን በማንበብ ድርጊቱ የተፈጥሮ ሀብቶችን የሚጠብቅ ከሆነ (✓) የሚጎዳ ከሆነ (X) ምልክት አድርጉ::

| | | |
|---|---|---|
| 1 | በክረምት ቆሻሻን ከጎርፍ ጋር ቀላቅሎ መድፋት:: | |
| 2 | እርከን መሥራት | |
| 3 | ሽንትን ከመፀዳጃ ውጭ መሽናት | |
| 4 | የእንስሳት ፅዳጅን መጠቀም | |

ሠ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ::

1. አምስት የባሕል ምሣሌዎችን ጥቀሱ::
2. ዋና ዋና የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች የሚባሉትን ዘርዝሩ::
3. ሁለቱ የግብርና ዋና ዋና ክፍሎች እነማን ናቸው?
4. የመጓጓዣ ጥቅሞች ከሆኑት ውስጥ አራቱን ጥቀሱ::

## ፍተሻ

ልታከናውኗቸው የምትችሏቸው ተግባራት የ (✓) ምልክት በመጠቀም አመልክቱ

1. የባህልን ምንነት እገልጻለሁ:: ☐
2. በወረዳችን የሚገኙ ባህላዊ ልማዶችን አብራራለሁ:: ☐
3. በወረዳችን የሚገኘውን የተፈጥሮ ሀብት ለመጠበቅና ለመንከባከብ የሚያግዙ ባህላዊ ልምዶችን እለያለሁ:: ☐
4. ባህላዊ ብዝኀነትን በሥነ ጥበብ አደንቃለሁ:: ☐
5. የአየር ንብረት በወረዳችን በሚንጸባረቁ ባህሎች ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ እገልጻለሁ:: ☐
6. በወረዳችን የሚከናወኑ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች አብራራለሁ:: ☐
7. ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በወረዳችን በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ የሚያደርሱትን ተጽዕኖ እለያለሁ:: ☐
8. የገበያ ምንነትን እገልጻለሁ:: ☐
9. የተፈጥሮ ሀብትና ምርቶቻቸው (ውጤቶቻቸው) በገበያ ላይ የሚኖራቸውን ተቀባይነት እገልጻለሁ:: ☐
10. በወረዳችን የሚገኙ የመጓጓዣ ዘዴዎችን አብራራለሁ:: ☐

# ምዕራፍ አምስት

# ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የትራፊክ ደንቦችን መግለጽና መጠቀም ትችላላችሁ፡፡
- በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ምልክቶችና በመድኃኒቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ትለያላችሁ፡፡

የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች፡-

5.1. የመንገድ ደኅንነት

5.2. ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ

## መግቢያ

ተማሪዎች! በሁለተኛ ክፍል በምዕራፍ አምስት ትምህርታችሁ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች በሚል ርዕስ ስለትራፊክ ደንቦች እና ኤች.አይ.ቪ./ ኤድስ ተምራችኋል፡፡ በሦስተኛ ክፍል ትምህርታችሁም ስለመንገድ ደኅንነትና ስለኤች. አይ.ቪ/ኤድስ ምልክቶችና በመድኃኒቶች መካከል ስላለው ግንኙነት ትማራላችሁ፡፡

## 5.1. የመንገድ ደኅንነት

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- የትራፊክ ደንቦችን መግለጽና መጠቀም ትችላላችሁ።

**ቁልፍ ቃላት**

- የመንገድ ደኅንነት
- የትራፊክ ደንቦች
- የትራፊክ አደጋ



ሥዕል 1 የመንገድ ደህንነት ደንቦች

ተማሪዎች! እነዚህን ስዕሎች ከተመለከታችሁ በኋላ ምን ምን ተረዳችሁ? የተረዳችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ።

**የቡድን ውይይት-1-**

ዓላማ፦ የትራፊክ ደንቦችን እና አጠቃቀምን መለየት

መመሪያ፦ 6 አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን በደብተራችሁ ላይ በመጻፍ በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. የምታውቋቸውን የመንገድ ደኅንነት ደንቦች ዘርዝሩ።
2. የመንገድ ደህንነት ደንቦችን አጠቃቀም አብራሩ።

## የመንገድ ደህንነት ደንቦች

የመንገድ ደህንነት ደንቦች ጤናማና የተረጋጋ የመንገድ እንቅስቃሴ ለማድረግ እንዲሁም አጠቃቀምን ለማሻሻል የሚጠቅሙ ሕጎች ናቸው፡፡ የመንገድ ደህንነት ደንቦችን በማክበር ራሳችንን ከተሽከርካሪ አደጋ መጠበቅ እንችላለን፡፡ ተማሪዎች! የትራፊክ አደጋ በተለያዩ ምክንያቶች ይደርሳል፡፡ በከፍተኛ ፍጥነት በማሽከርከር ለእግረኞች ቅድሚያ ባለመስጠት እንዲሁም በእግረኞች ቸልተኝነት ሊከሰት ይችላል፡፡ ስለዚህ የመንገድ ደኅንነት ደንቦችን በመረዳት ራሳችንን እና ቤተሰቦቻችንን ከተሽከርካሪ አደጋ መጠበቅ አለብን፡፡ የመንገድ ደኅንነት ደንቦች በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም

1. የእግረኞች የመንገድ ደህንነት ደንቦች
2. የአሽከርካሪ የመንገድ ደህንነት ደንቦች ናቸው፡፡

### 1. የእግረኞች የመንገድ ደኅንነት ደንቦች

### ሀ. የትራፊክ መብራትን መመሪያ ማክበር፡፡

የትራፊክ ማስተላለፊያ መብራቶች በሁለት የሚከፈሉ ሲሆኑ እነርሱም፡-

1. የእግረኛ ማስተላለፊያ መብራት
2. የተሽከርካሪዎች ማስተላለፊያ መብራት ናቸው፡፡

#### 1. የእግረኛ ማስተላለፊያ መብራት



ሥዕል 2 የእግረኛ ማስተላለፊያ መብራት

እግረኞች ከአደጋ ነፃ ሆነው መንገድን እንዲያቋርጡ የሚረዱ ሲሆኑ በቀለም ብዛታቸው ሁለት ዓይነት ናቸው። እነርሱም ቀይ እና አረንጓዴ ናቸው። የእግረኛ ማስተላለፊያ መብራቶች በውስጣቸው የእግረኛ ምስል አላቸው።

ቀይ የእግረኛ ምስል ያለበት መብራት ሲበራ እግረኞች መንገድ እንዲያቋርጡ አይፈቀድላቸውም። አረንጓዴ የእግረኛ ምስል ያለበት መብራት ሲበራ ደግሞ እግረኞች መንገድ እንዲያቋርጡ ይፈቀድላቸዋል።


### 2. የተሽከርካሪዎች ማስተላለፊያ መብራት



ሥዕል 3. የትራፊክ መብራት

የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ መብራት ቀለማት ሦስት ናቸው። እነርሱም አረንጓዴ፣ቢጫና ቀይ ናቸው። ቀለማቱ የተለያዩ መልዕክቶችን ያስተላልፋሉ። ተማሪዎች የሦስቱን ቀለማት ትርጉም በዝርዝር ስንመለከት በሥዕል 3 እንደተመለከታችሁት አረንጓዴ መብራት ብቻ ሲበራ ተሽከርካሪዎች እንዲሄዱ እና እግረኞች እንዲቆሙ የሚያመለክት ነው። ቀይ መብራት ሲበራ እግረኞች እንዲሄዱ (እንዲያቋርጡ) እና ተሽከርካሪዎች እንዲቆሙ የሚያመለክት ነው። ቢጫ መብራት ሲበራ ማስጠንቀቂያ ሲሆን ከቀይ ወደ አረንጓዴ እና ከአረንጓዴ ወደ ቀይ ትዕዛዝ መሸጋገሪያ ጊዜ የሚሰጥ ነው። ስለዚህ የመኪና መንገድ ማቋረጥ የምንችለው ቀይ ሲበራ ብቻ ነው። አረንጓዴው ሲበራ መንገድ ማቋረጥ የለብንም።

ለ. እግረኞች ሁልጊዜ የመንገዱን የግራ መስመር ይዘው መሄድ አለባቸው።



ሥዕል 4. የግራ መስመርን ይዘው የሚሄዱ እግረኞች

ሐ. መንገድ በምናቋርጥበት ጊዜ ተሽከርካሪ መምጣት አለመምጣቱን መቃኘት ተገቢ ነው።

መ. የቆመ ተሽከርካሪ ተከልሎ ማቋረጥ የለብንም።

ሠ. መንገድ በምናቋርጥበት ጊዜ አለማውራት እና አለመጫወት።

ረ. መንገድ በምናቋርጥበት ጊዜ ንቁ መሆን።

ሰ. የአስፋልት መንገድ ስናቋርጥ ለእግረኞች ማቋረጫ በተሰመረው ዜብራ ብቻ መጠቀም።



ሥዕል 5. የአስፋልት መንገድ ሲያቋርጡ ዜብራን የሚጠቀሙ ልጆች

በተሽከርካሪ ውስጥ ስንሆን የምንከተላቸው የትራፊክ ደንቦች አሉ፡፡እነርሱም፡-

ሀ. በመኪና ስንጓዝ የመኪና ቀበቶን ማሠር ያስፈልጋል፡፡



ሥዕል 6. በመኪና ሲጓዙ ቀበቶ ያሰሩ ልጆች

ለ. ከተሽካርካሪ ስንወርድ ከተሽከርካሪው በስተቀኛችን ባለው በር ብቻ መውረድ፡፡

ሐ. ተሽካርካሪ በደንብ ሳይቆም አለመውረድና አለመሳፈር፡፡

ተማሪዎች! ተሽከርካሪ በምንጠቀምበት ጊዜ ተሽከርካሪው በደንብ መቆሙን ሳናረጋግጥ መውረድም ሆነ መሳፈር የለብንም፡፡ ምክንያቱም ተሽከርካሪው እየተንቀሳቀሰ ከሆነ ለአደጋ እንጋለጣለን፡፡



ሥዕል 7 ተሽከርካሪው ሳይቆም በመውረድ የተፈጠረ አደጋ

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የትራፊክ ደንቦችን እና ሌሎች የትራፊክ መመሪያዎችን ሁልጊዜ ማክበር አለብን፡፡

ተግባር 1.

በምልክት የመግለፅ ጨዋታ

ዓላማ፡- የእግረኞች የመንገድ ደኅንነት ደንቦችን በምልክት መግለጽ

መመሪያ፡-ተማሪዎች! እኩል የአባላት ብዛት ያሉት አራት ቡድን ከመሰረታችሁ በኋላ ከየቡድናችሁ ሦስት ተማሪዎችን በመምረጥ ከመምህራችሁ በሚስጥር የመንገድ ደኅንነት ደንቦችን በማየት በምልክት እንዲያስረዱ በማድረግ የቡድኑ አባላት ደንቦቹን መገመት፡፡ በመጨረሻም ብዙ የመለሰ ቡድን አሸናፊ ይሆናል፡፡

## 2 የአሽከርካሪ የመንገድ ደኅንነት ደንቦች

እግረኞች ከሚያከብሯቸው ደንቦች በተጨማሪ አሽከርካሪዎች ሊያከብሯቸው የሚገቡ የአሽከርካሪ የመንገድ ደኅንነት ደንቦች አሉ ፡፡ እነርሱም፡-

### ሀ. የትራፊክ ምልክቶችን ማክበር፡፡

የትራፊክ ምልክቶች ለመንገድ ደኅንነት አስፈላጊ ሲሆኑ የመንገድ ዳር ምልክቶች በማለት ሊገለጹ ይችላሉ፡፡የመንገድ ዳር ምልክቶች በሚያስተላልፉት መልዕክት መሰረት በሦስት ይከፈላሉ፡፡እነርሱም፡-

1. የሚያስጠነቅቁ
2. የሚቆጣጠሩ እና
3. መረጃ የሚሰጡ ናቸው፡፡

#### 1. የሚያስጠነቅቁ

አሽከርካሪዎች ስለሚያጋጥማቸው የመንገድ ሁኔታ አስቀድመው እንዲያውቁ የሚረዳ ነው፡፡ ለምሳሌ:-



ሥዕል 8/ሀ/የሚፈናጠር ድንጋይ ስላለ ተጠንቀቅ



/ለ/አደገኛ መንገድ ስለሚያጋጥምህ ተጠንቀቅ

2. የሚቆጣጠሩ፡- የሚቆጣጠሩ የመንገድ ዳር ምልክቶች የሚከለክሉ፣ቅድሚያ የሚያሰጡ እና የሚያስገድዱ ናቸው፡፡ የሚከለክሉ ለምሳሌ





ሥዕል 9 ሀ/ ብስክሌት እያሽረከሩ ማለፍ የተከለከለ ለ/ ለእግረኛ ማለፍ የተከለከለ

ቅድሚያ የሚያሰጡ፡- ለምሳሌ





ሥዕል 10 ሀ/ የቅድሚያ መጨረሻ ለ/ ቆመህ ቅድሚያ ስጥ

የሚያስገድዱ የመንገድ ዳር ምልክቶች፡- ለምሳሌ



ሥዕል 11 ለብስክሌት ብቻ የተፈቀደ

## 3. መረጃ ሰጪ የመንገድ ዳር ምልክቶች

በቀጥታ የተለያዩ መረጃዎችን የሚሰጥና አቅጣጫ የሚያመለክት ነው፡፡

በቀጥታ መረጃዎችን የሚሰጡ የመንገድ ዳር ምልክቶች ለምሳሌ፡- ሆስፒታል፣ ሆቴል፣ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ እና የመሳሰሉትን ያመለክታሉ፡፡




ሥዕል 12 መረጃ ሰጪ የመንገድ ዳር ምልክቶች

አቅጣጫ አመልካች የመንገድ ዳር ምልክቶች በተለያዩ አቅጣጫ የሚያስኬዱ

መንገዶችን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡




ሥዕል 13 አቅጣጫ አመልካች የመንገድ ዳር ምልክት

## ለ. የትራፊክ ፖሊስ የእጅ ምልክትን ማክበር እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡




ሥዕል 14 የትራፊክ ፖሊስ የእጅ ምልክቶች

ተግባር -2-

የግል ስራ

ዓላማ፡-ያልተከበሩ የመንገድ ደኅንነት ደንቦችን መለየት

መመሪያ፡-ተማሪዎች! ከዚህ በታች ያለውን ስዕል በመመልከት ከ10 እስከ 20 የሚሆኑ ስህተቶችን በመፈለግ ለተማሪዎች አብራሩ፡፡ በመጨረሻም ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ፡፡



ሥዕል 15 የመንገድ ደኅንነት ጥሰት

ተግባር -3-

እንግዳ መጋበዝ

ዓላማ፡- የትራፊክ ደንቦችን አጠቃቀምን ከባለሙያ መረዳት

መመሪያ፡- በመምህራችሁ የተጋበዙትን እንግዳ በክብር በመቀበል የሚሰጡትን ገለፃ በጥሞና በመከታተልና ጥያቄዎችን በማንሳት ከእንግዳው ጋር በትራፊክ ደንቦች አጠቃቀም ዙሪያ ውይይት አድርጉ፡፡ በመጨረሻም ከውይይቱ ያገኛችሁትን ፍሬ ሐሳብ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡




ሥዕል 16. ከፍተኛ ጉዳት ያስከተለ የትራፊክ አደጋ

ተግባር-4-

የሚና ጨዋታ

ዓላማ፦ የትራፊክ አደጋ የሚያስከትለውን ጉዳቶች መግለፅ

መመሪያ፦ ከ5-7 አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በቡድናችሁ በመሆን አንድ ተማሪ ትራፊክ ፖሊስ ሌሎች ደግሞ መንገድ ላይ ኳስ የሚጫወቱ ልጆች በመሆን የሚፈጠር አደጋን መነሻ በማድረግ ያስከትለውን ጉዳት የሚያሳይ የሚና ጨዋታ ካዘጋጃችሁ በኋላ ልምምድ በማድረግ በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡ተማሪዎች! ከሚና ጨዋታው ምን ተረዳችሁ? የመኪና አደጋ በህፃናትና በቤተሰብ ላይ የሚያመጣው ጉዳት ምንድን ነው? ለመምህራችሁ አብራሩ፡፡

የትራፊክ አደጋ ማንኛውንም የማኅበረሰብ ክፍል ያጠቃል፡፡ አንድ የትራፊክ አደጋ ከፍተኛ የአካል፣ የሕይወትና የንብረት ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡ የትራፊክ አደጋ ሲከሰት በተሽከርካሪው ውስጥ ባሉ ሰዎች ብቻ ሳይሆን በቤተሰብ፣ በማኅበረሰብና በሀገር ላይ ጉዳት ያደርሳል፡፡



ሥዕል 17 በመንገድ ላይ ኳስ እየተጫወቱ የመኪና አደጋ ሲደርስባቸው

ተማሪዎች! ሥዕሉን እንዳያችሁት በመንገድ ላይ ኳስ መጫወት በቤተሰብና በሕጻናት ላይ ጉዳት ያደርሳል፡፡ ለምሳሌ፡- ሕፃናት ለአካል ጉዳተኝነትና ለሞት ይጋለጣሉ፡፡ ስለዚህ በመኪና መንገድ ላይ ኳስ መጫወት የለብንም፡፡

ተግባር -5-

የግል ሥራ

ዓላማ፡ የትራፊክ አደጋ የሚያስከትለውን ችግር መተንተን

መመሪያ፡ ተማሪዎች! በአከባቢያችሁ የተከሰተን አንድ እውነተኛ የትራፊክ አደጋን በማጥናትና ታላላቆቻችሁን በመጠየቅ ያስከተለውን ችግር በመተንተን በክፍል ውስጥ አብራሩ፡፡

## መልመጃ 5.1

ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች በማንበብ ትክክል ከሆነ"እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡

1. የመንገድ ደኅንነትን ለመጠበቅ የትራፊክ ደንቦችን ማክበር አለብን፡፡
2. መንገድ ከማቋረጣችን በፊት ተሽከርካሪዎች አለመኖራቸውን ማረጋገጥ አለብን፡፡
3. በዜብራ (በእግረኛ ማቋረጫ) ላይ ኳስ መጫወት እንችላለን፡፡
4. እግረኛ የመንገዱን የግራ መስመር ይዞ መሄድ አለበት፡፡
5. ስለመንገድ ደኅንነት የሚመለከተው የትራፊክ ፖሊስን ብቻ ነው፡፡
6. የትራፊክ አደጋ በሁሉም ዕድሜ ክልል ያሉ ሰዎችን ይጎዳል፡፡


ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. የትራፊክ ደንቦችን ማወቅና መጠቀም ለሰው ልጅ የሚሰጠው ጥቅም ምንድነው?
2. ሥዕሉን በማየት የትራፊክ መብራት ቀለማትን ትርጉም ግለጹ፡፡

ሀ. አንድ ቁጥር ምን ያመለክታል?

ለ. ሁለት ቁጥር ምን ያመለክታል?

ሐ. ሦስት ቁጥር ምን ያመለክታል?




## 5.2. ኤች. አይ. ቪ. / ኤድስ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- በኤች. አይ. ቪ. እና ኤድስ ምልክቶችና በመድኃኒቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ትለያላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ኤች. አይ. ቪ
- ኤድስ

ተማሪዎች! በሁለተኛ ክፍል ትምህርታችሁ ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የተማራችሁትን ታስታውሳላችሁ? የምታስታውሱትን የኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ የመተላለፊያ እና የመከላከያ መንገዶችን ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያይታችሁ ከዚህ በታች በሰንጠረዥ የተቀመጡትን ዓረፍተ ነገሮች በመጠቀም ባዶ ቦታ ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ መልሳችሁን በደብተራችሁ ላይ ጻፉ፡፡

| | |
|---|---|
| የደም ንክኪ ሲኖር | አብሮ መመገብ |
| አብሮ መጫወት | የጥርስ ቡርሽን በጋራ መጠቀም |
| ስለታማ ነገሮችን በጋራ መጠቀም | መጽሐፍትን በጋራ መጠቀም |

| ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሚያስተላልፉ | ኤች. አይ.ቪ/ኤድስ የማያስተላልፉ |
|---|---|
| | |
| | |
| | |

የቡድን ውይይት-2-

ዓላማ፡- የኤች. አይ. ቪ / ኤድስ ምንነትና ምልክቶችን መለየት

መመሪያ፡- ከ5-7 ተማሪዎችን የያዘ ቡድን መስርታችሁ ከዚህ በታች ባሉት የመወያያ ነጥቦች ላይ በመወያየት በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

የመወያያ ነጥቦች

- ኤች. አይ. ቪ.. ምንድን ነው?
- ኤድስ ማለት ምን ማለት ነው?
- የኤች. አይ. ቪ./ ኤድስ ምልክቶችን ዘርዝሩ?

ኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ሲሆን የሰዎችን በሽታ የመከላከል አቅም እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡ ሰዎችም በልዩ ልዩ በሽታዎች በመጋለጥ ይታመማሉ፡፡

ኤች.አይ.ቪ.፡- ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍ፣ ከቫይረሶች ውስጥ የሚመደብ፣ በደም ውስጥ የሚራባ፣ ሰውነታችን በሽታን እንዲቋቋም የሚያስችሉትን ሕዋሶች በማጥቃት የሰውነታችንን በሽታን የመከላከል ስርዓት የሚያዳክምና የኤድስን ሕመም የሚፈጥር ቫይረስ ነው፡፡ ስለዚህ ኤች. አይ. ቪ የኤድስ ሕመም መንስኤ የሆነ ቫይረስ መጠሪያ መጠሪያ ስም ነው፡፡

ኤድስ የሚለው ምህፃረ ቃል የተወሰደው ከእንግሊዘኛ ስያሜ ሲሆን መሰረታዊ ሀሳቡ ወደ አማርኛ ሲመለስ ከሰው ወደ ሰው የተላለፈ፣ የተፈጥሮ የሰውነት የበሽታ የመከላከያ አቅምን የሚያዳክምና ሕመም ምልክቶች ማለት ነው፡፡

ኤድስ በራሱ ሕመም ሳይሆን የሰውነት ሕመም መከላከል ስርዓት በማውደሙ ምክንያት ለሞት የሚያበቁ የተለያዩ ሕመም ዓይነቶች የመጋለጥ ሁኔታ ነው፡፡ ስለዚህ ኤድስ ማለት በኤች.አይ.ቪ. ምክንያት የሚመጣና ሰውነትን ለተለያዩ ሕመሞች በቀላሉ እንዲጋለጡ የሚያደርግ ሕመም ነው፡፡

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ፈፅሞ ለማዳን ወይም ከደም ውስጥ ቫይረሱን ሊያጠፋ የሚችል መድኃኒትም ይሁን ክትባት አልተገኘለትም፡፡ ነገር ግን ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው ሰዎች ለሌላ ሕመም እንዳይጋለጡ እና የቫይረሱ መራባትን ለመቆጣጠር የሚያስችል መድኃኒት አለ፡፡ ይሁን እንጂ መድኃኒቱ ፈዋሽ አይደለም፡፡ ስለዚህ ጠቃሚው መንገድ በቫይረሱ እንዳንያዝ አስቀድሞ መጠንቀቅ ነው፡፡

ተግባር-6-

የግል ሥራ

ዓላማ፡- በኤች. አይ. ቪ / ኤድስ ምልክቶች እና በመድኃኒቶች መከላከል ያለውን ግንኙነት መለየት

መመሪያ፡- ተማሪዎች! ከታላላቆቻችሁና ከቤተሰቦቻችሁ ጋር በመወያየት ስለ ኤች. አይ. ቪ / ኤድስ ምልክቶች እና መድኃኒቶች መካከል ስላለው ግንኙነት በፅሑፍ በማዘጋጀት በክፍል ውስጥ ካቀረባችሁ በኋላ የጋራ ውይይት በማድረግ የማጠቃለያ ሀሳብን በደብተራችሁ ላይ ጻፉ፡፡

ተማሪዎች! የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ምልክቶችን ብቻ በማየት በደም ውስጥ ኤች. አይ.ቪ. ቫይረስ አለ ማለት አይቻልም፡፡ በደም ውስጥ ኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ መኖሩን ማረጋገጥ የሚቻለው በምርመራ ብቻ ነው፡፡

የኤች. አይ. ቪ./ኤድስ ምልክቶች የሚባሉት እንደ ማስመለስ፣ ክብደት መቀነስ፣ ከፍተኛ ላብ ማላብ፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስ፣ ተቅማጥ፣ ሳል፣ ትኩሳት፣ የጉሮሮ ቁስለት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ምልክቶች ደረጃ በደረጃ እየተባባሱ ስለሚሄዱ መድኃኒቶችን እንደየሕመሙ ደረጃ መጠቀም ተገቢ ነው፡፡

## መልመጃ 5.2

ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች በማንበብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡

1. ኤች.አይ.ቪ. እና ኤድስ ልዩነት አላቸው፡፡
2. ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ፈዋሽ መድኃኒት የለውም፡፡
3. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በማኅበረሰብ ላይ ጉዳት አያደርስም፡፡
4. ኤች. አይ. ቪ /ኤድስ በደም ውስጥ መኖሩን ማረጋገጥ የሚቻለው በምርመራ ብቻ ነው፡፡
5. የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ምልክቶች እና መድኃኒቶች ግንኙነት የላቸውም፡፡

ለ. በ 'ሀ' ስር የቀረቡትን በ 'ለ' ስር ከተዘረዘሩት አማራጮች ጋር በትክክል አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የኤች.አይ.ቪ. መተላለፊያ | ሀ. ኤች. አይ. ቪ. |
| 2. የኤድስ ሕመም መንስኤ | ለ. አብሮ መጫወት |
| 3. የኤድስ መከላከያ | ሐ. ስለታማ ነገሮችን በጋራ አለመጠቀም |
| 4. ኤች.አይ.ቪ. የማይተላለፍበት | መ. የደም ንክኪ |

## ማጠቃለያ

❖ ከመንገድ ደሕንነቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው የትራፊክ ደንቦችን ማወቅና መጠቀም ነው፡፡

❖ የመንገድ ደኅንነት በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም፡- የእግረኞችና የአሽከርካሪ ደንቦች በመባል ይታወቃሉ፡፡

❖ የእግረኞች የመንገድ ደኅንነት ደንቦች የሚባሉት የትራፊክ መብራት መመሪያን ማክበር፣ የግራ መስመር ይዞ መሄድ፣ መንገድ ስናቋርጥ ተሽከርካሪ አለመምጣቱን ማረጋገጥ፣ የቆመ ተሽከርካሪ ተከልሎ አለማቋረጥና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

❖ የአሽከርካሪ የመንገድ ደህንነት ደንቦች የሚባሉት የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ መብራት መመሪያን ማክበር፣ የትራፊክ ምልክቶችን ማክበር፣ የትራፊክ ፖሊስ የእጅ ምልክቶችን ማክበርና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

❖ የትራፊክ ማስተላለፊያ መብራቶች በሁለት የሚከፈሉ ሲሆኑ እነርሱም፡ -የእግረኛ ማስተላለፊያ መብራትና የተሽከርካሪዎች ማስተላለፊያ መብራት ናቸው፡፡

❖ የመንገድ ዳር ምልክቶች በሚያስተላልፉት መልዕክት ልዩነት ምክንያት በ ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም የሚያስጠነቅቁ፣ የሚቆጣጠሩ እና መረጃ የሚሰጡ ናቸው፡፡

❖ ኤች. አይ. ቪ. ለኤድስ ሕመም መንስኤ የሆነ ቫይረስ ሲሆን ኤድስ ደግሞ በኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ምክንያት የሚመጣ ሕመም ነው፡፡

❖ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስን ለመቋቋም እንደሕመሙ ደረጃ እና ምልክቶች መድኃኒቶችን መውሰድ አለበት፡፡ ስለዚህ የኤች. አይ. ቪ. /ኤድስ ምልክቶች እና መድኃኒቶች ግንኙነት አላቸው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች በማንበብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ::**

1. ኤች. አይ. ቪ /ኤድስ እና የመንገድ ደህንነት ከድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች ውስጥ ይመደባሉ::
2. የትራፊክ ደንቦችን ማወቅና መጠቀም ሁላችንንም ይመለከታል::
3. የኤች.አይ.ቪ /ኤድስ መድኃኒቶች ቫይረሱ በፍጥነት እንዳይረባ ያደርጋሉ::
4. የኤች. አይ. ቪ /ኤድስ  ምልክት ደረጃዎች አሉት::
5. በመኪና አደጋ ምክንያት አካል ጉዳተኝነት ሊፈጠር ይችላል::

**ለ. በ 'ሀ' ስር የቀረቡትን በ 'ለ' ስር ከተዘረዘሩት አማራጮች ጋር በትክክል አዛምዱ::**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ተሽከርካሪ በሚጓዝበት በስተግራ እና በስተቀኝ በኩል ያለ ነው:: | ሀ. ዜብራ |
| 2. ለአሽከርካሪዎችና ለእግረኞች መመሪያ የሚሰጥ ነው | ለ. የትራፊክ አደጋ |
| 3. የእግረኛ ማቋረጫ መስመሮች | ሐ. የትራፊክ መብራት |
| 4. አሽከርካሪዎችና እግረኞች በሚፈጥሩት ስሕተት የሚከሰት ነው | መ. የእግረኛ መንገድ |

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።

1. ኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ ጉዳት የሚያደርሰው በየትኛው ላይ ነው?

   ሀ. በንብረት  ለ. በግለሰብ  ሐ. በማሕበረሰብ  መ. ሁሉም

2. የትራፊክ ደንብ ማክበርን የማያሳየው የቱ ነው?

   ሀ. በመንገድ ላይ ኳስ መጫወት።

   ለ. እግረኛ የግራ መስመሩን ይዞ መሄድ።

   ሐ. የትራፊክ ምልክቶችን መጠቀም።

   መ. የቆመ ተሽከርካሪን ተከልሎ አለማቋረጥ።

3. የኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ መተላለፊያ መንገድ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. አብሮ መጫወት  ለ. ስለታማ ነገሮችን በጋራ መጠቀም

   ሐ. የጋራ መፀዳጃ ቤቶችን መጠቀም  መ. በጋራ መማር

4. ኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ የሚያጠቃው የትኛውን የሕብረተሰብ ክፍል ነው?

   ሀ. ህፃናትን  ለ. አዛውንትን  ሐ.ወጣቶችን  መ.ሁሉም

5. ለትራፊክ አደጋ መከሰት ምክንያት ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?

   ሀ. ጠጥቶ ማሽከርከር

   ለ. በከፍተኛ ፍጥነት ማሽከርከር

   ሐ. በእግረኞች ቸልተኝነት

   መ. ሁሉም

## ፍተሻ

ልታከናውኗቸው የምትችሏቸውን ተግባራት ለመግለፅ ይህን (✓) ምልክት በሳጥን ውስጥ በማስቀመጥ አመልክቱ

1. የትራፊክ ደንቦችን መግለጽና መጠቀም እችላለሁ። ☐
2. በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ምልክቶችና በመድኃኒቶች መካከል ያለውን ግንኙነት እለያለሁ። ☐